# ትግላችን




# ትግላችን

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

ወርኃዊ መጽሔት

አዘጋጅ — አንዳርጋቸው አሰግድ

1 Berlin 19
Harbigstr. 1

ታህሣሥ ፲፱፻፷፮

ቁጥር ፩

ዋጋው — ፩ የኢት ብር

ይዘት፤ ገጽ


| ይዘት፤ | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | |
| ርዕሰ—አንቀጽ፤ | ፩ |
| ከአፀፀቢ ቂፋ፡ አስኩማፕ፡ ወልደ | ፭ |
| ያገር፡ቤት፡ወሬ | ፮ |
| ዘመናዊ፡መኳንንትና፡የፊውዳሉ፡ ሥርዓት | ፰ |
| የመንግሥቱን፡ጋዜጣ፡ስናገላብጥ | ፱ |
| ለትግላችን፡አዘጋጅ፡ደብዳቤ | ፲፯ |
| ዩኒቨርሲቲ፡ለሚገቡ፡የታደሉ፡ጽሑፍ | ፳ |


## መቅድም፤

እንደ፡ደንቡ፡ቢሆን፤«ትግላችን»፡ከሁለት፡ቀደም፡ብሎ፡መውጣት፡ነበረበት። አዘጋጅ፡ቦርዱም፡በተቻለ፡መጠን፡ቀደም፡ብሎ፡ለማውጣት፡ሳይደክም፡አልቀረም።

ነገር፡ግን፤እንደምታዩት፤በዚህ፡ዓመት፡«የትግላችን»፡አቀራረብ፡ከልክ፡በላይ፡ተለውጧል። ባለፈው፡ዓመት፡በጅ፡እየተጻፈ፡በመውጣቱ፡አዘጋጆች፡የነበረባቸውን፡ድካምና፡አንባቢዎች፡የደረሰባቸውን፡ችግር፡ሳናስታውሳችሁ፡አንቀርም። ይህንንም፡ችግር፡ለማስወገድ፡መጽሔቶች፡በጅ፡እየተጻፉ፡በመውጣት፡ፈንታ፡ታትመው፡እንዲወጡ፡አዘጋጅ፡ቦርዱ፡ከሰበበት፡ብዙ፡ጊዜ፡ቢያልፍም፡ቅሉ፡ይኸው፡አሁን፤ለመጀመሪያ፡ጊዜ፡«ትግላችን»፡ታትሞ፡ወጥቷል። በተጨማሪ፡«ትግላችን»፡የሚይዛቸውን፡መሠረተ—አሳቦች፡አጠቃሎ፡የሚያሳይ፤የተማሪዎችን፡«ዓላማ»፡የሚገልጽ፡አርማ፡«በትግላችን»፡ሽፋን፡ላይ፡እንዲውል፡ሆኗል። እስካሁን፡የዘገየበት፡ዋናው፡ምክንያት፡በዚህ፡መልክ፡ለማቅረብ፡ብዙ፡መሰናዶ፡ያስፈልገው፡ስለነበር፡ነው።

መሰናዶው፡በሚደረግበት፡ጊዜ፡ብዙ፡እንቅፋቶች፡ገጥመውን፡ነበር። ነገር፡ግን፡በአውሮፓ፡የኢትዮጵያ፡ተማሪዎች፡ማኅበር፡ሥራ፡አስኪያጅ፡ኮሚቴና፡አዘጋጅ፡ቦርዱ፡«ራስን፡መቻል»፡የሚለውን፡መሠረታዊ፡አሳብ፡መሪ፡ቃል፡በማድረግ፡ተባብረው፡ስለሠሩ፤አንዳንድ፡አባላት፡ሙሉ፡ድጋፋቸውን፡ስለሰጡ፡አብዛኞቹን፡እንቅፋቶች፡በቀላሉ፡አሸንፎ፡ለማለፍ፡ተችሏል።

በቆራጥነት፤በትጋትና፡በመተባበር፡ከተሠራ፤ማንኛውንም፡ነገር፡ከተፈለገው፡ግብ፡ለማድረስ፡ይቻላል። ትግላችንን፡በቆራጥነት፡እንቀጥል! እናሸንፋለን።

---

በአሁኑ፡መልክ፡የማውጣት፡ልምምድ፡ስላልነበረን፤በጥድፊያ፡ማውጣት፡ስላስፈለገ፡መጽሔቱ፡አልፎ፡አልፎ፡አንዳንድ፡የአጻጻፍ፡ስሕተቶችን፡(ለምሳሌ፡ነጥቦችንና፡ፊደላትን፡ያለቦታቸው፡ማስገባት፡ወይም፡መግደፍ፡ወዘተ፡)ይዞ፡ይሆናል። ለወደፊቱ፤ከትንሽ፡ልምምድ፡በኋላ፤እነዚህ፡ስህተቶች፡እንደሚወገዱ፡ተስፋ፡ስናደርግ፤ለጊዜው፡ስህተቶችን፡በትዕግስት፡እያረሙ፡እንዲያነቡ፡አንባቢዎችን፡እንጠይቃለን።

ርዕስ—እንቀጽ፤

<u>በአውሮፓ፡የኢ፡ት፡ተ፡ማ፡ማ፡፰ኛ፡ጠ፡ጉ፡ባኤ፡—</u>

እንደአውሮፓ፡አቆጣጠር፡ከሐሌ፡፲፱—፲፰፡፲፱፻፷፰ ዓ፡ም፡በዛግሬብ፡ዩጐዝላቢያ፡የተደረገው፡በአ፡የኢ፡ት፡ተ፡ማ፡ማ፡፰ኛ፡ጠቅላላ፡ጉባዔ፡ዘንድሮም፡አንዳንድ፡ትላልቅ፡ድሎችን፡ተቀዳጅቷል፡፡ይጠበቁ፡ከነበሩት፡አ ሥራስድስት፡ማኅበራት፡ውስጥ፡ያሥራሦስቱ፡ማኅበራት፡ሐላፊዎች፡ወይም፡ወኪሎች፡ሲገኙ፡እንደዚሁም፡በማኅበሩ፡ታሪክ፡ውስጥ፡ለመጀመሪያ፡ጊዜ፡በሰሜን፡አሜሪካ፡ያሉ፡የትግል፡ጓዶቻችን፡አንድ፡መልክተኛ—ጓድ፡ሐጐስ፡ገ፡የሱስን—ልከው፡ነበር፡፡

አድኃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡የማኅበሮቻችንን፡አንድነት፡ለማፍረስና፡ትግላችንን፡ለማድከም፡ወስዶት፡የነበረውን፡እርምጃ፡ሁሉ፡ስናስታውስ—ለምሳሌ፡በያገሩ፡የተማሪዎቹን፡መደጐሚያ፡በመቀነስ፤የፓስፖርት፡ችግርችን፡እየፈጠሩ፡ተማሪዎች፡ከሉበት፡እንዳይንቀሳቀሱ፡ለማድረግ፡በመሞከር፤ስለማኅበሩ፡አመራር፡ከንቱና፡ሐሰተኛ፡ወሬዎችን፡በማስወራት፡ወዘተ፡—ያሥራሦስቱ፡ማኅበራት፡መገኘትና፡የጉባዔው፡መልካም፡ውጤት፡መስጠት፡እንደትልቅ፡ድል፡ሊቆጠር፡ይገባዋል፡፡በፖለቲካው፤በድርጅቱና፡በቆራጥነቱ፡አንድነቱን፡አጠንክሮና፡በትግል፡እሳት፡ተፈትኖ፡የወጣ፡ማኅበር፡ሆኗል፡ለማለት፡ይቻላል፡፡የጠላቶቹ፡ተንኮል፡አሁንም፡እንደ ገና፡ከመክሸፉም፡በላይ፡የማኅበሩን፡ጥንካሬ፡ጭምር፡አስከትሏል፡፡

ነገር፡ግን፡የማኅበሩ፡ጥንካሬና፡ቆራጥነት፡በጨመረ፡ቁጥር፤የማኅበርተኞቹ፡የመንፈስ፡ንቃትና፡ዝግጁነት፡እየዳበረ፡በሄደ፡ቁጥር፤ያድኃሪ፡ጠላቶችም፡ተንኮል፡በዓይነትና፡በብዛት፡እየጨመረ፡ይሄዳል፡፡የሕዝብን፡ወገን፡በመምረጥ፡ላዲስ፡ሕዝባዊት፡ኢትዮጵያ፡የሚታገል፡ሁሉ፡ድምጽ፡እንዲታፈን፡ለማድረግ፡አድኃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡በማንኛውም፡የተንኰል፡ዘዴ፡ከመጠቀም፡አይመለስም፡፡አንዳንዴ፡በማስፈራሪያ፤አንዳንዴ፡በድለላ፡ይጠቀማል፤መንፈሰ—ደካሞችን፡በቀላሉ፡እንደሕፃን፡ያታልላቸዋል፤አድር—ባዮችን፡በቀጥታ፡ይገዛቸዋል፤በሰላዮቹና፡በቡችሎቹ፡በመጠቀም፡በወሬና፡በዛቻ፡ለመበታተን፡ይሞክራል፡፡አድኃሪዎች፡እስከዕለተ—ፍጻሜያቸው፡ድረስ፡ይፍጨረጨራሉ፡እንጅ፡«በመልካም፡ፈቃዳቸው»፡ሥል ጣንን፡ለሕዝብ፡አያስረክቡም፤ሕዝቡ፡የወደፊት፡ዕድሉን፡በፈለገው፡መንገድ፡እንዲቀይሰው፡አይፈልጉም፤ይህ፡መሠረታዊ፡ባሕሪያቸው፡ስለሆነ፡አድኃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡ከዚህ፤ሕግ፡ሊያመልጥ፡አይችልም፡፡



ይህ፡ከሆነ፡ማኅበራችን፡ካለፈው፡ትግሉ፡ተገቢውን፡ትምህርት፡በመቅሰም፤ስሀተቶችን፡በማረምና፡የጠላትን፡ተንኮል፡ነቅቶ፡እየተጠባበቁ፡በማክሸፍ፤ትግሉን፡ወደከፍተኛ፡ደረጃ፡ለማድረስ፡በታላቅ፡ትጋትና፡ጥንቃቄ፡ወደፊት፡መገስገስ፡ይኖርበታል፡፡በዚህ፡መሠመር፡የጉባዔውን፡ዋና፡ዋና ውጤቶች፡መመዝገብ፤የነበሩትን፡ችግሮች፡ወይም፡ጉድለቶች፡መመልከትና፡ስለማኅበሩ፡የወደፊት፡እርምጃ፤ማሰብ፡ያስፈልጋል፡፡

የማኅበሩን፡የወደፊት፡ግስጋሴ፡ሊያረጋግጥ፡የሚችለው፡የንቁ፡ማኅበርተኞች፡ትጋትና፡ቆራጥነት፡ነው፡፡እነዚህ፡ትጉ፤ቆራጥና፡ባለሕሊና፡ማኅበርተኞች፡ያውሮፓውን፡ማኅበር፡የአባላት፡ዓይነት፡ከተመለከቱ፡በኋላ፡በርከት፡ያሉት፡ማኅበርተኞች፡በሬቮሉሽናዊ፡ሰንደቅ፡ዓላማ፡ሥር፡ሊሰለፉ፡የሚችሉበትን፡ዘዴ፡ሳይታክቱ፤መፈለግ፡አለባቸው፡፡

እንግዲህ፡በያመቱ፡ጠቅላላ፡ጉባዔ፡ሲደረግ፡ከስብሰባው፡ላይ፡የሚገኙ፡ምን፡ዓይነት፡አባሎች፡ናቸው?

ከሚመጡት፡አባሎች፡ጥቂቶቹ፡በቀጥታ፡ከፊውዳላዊው፡ዓለም፡አብራክ፡የወጡ፤የፊውዳላዊ፡ርእዮተ—ዓለማቸውን፡ለመለወጥ፡ያልሞከሩ፡ወይም፡ሞክረው፡ያልቻሉ፤ከሕፃን፡አንጐላቸው፡ጋር፡እንዲጣበቅ፡ከተሰጣቸው፡አደንቋሪ፡ትምህርት፡ነፃ፡ለመውጣት፡ያልቻሉ፡ናቸው፡፡እነዚህ፡ሰዎች፡«ኢትዮጵያ»፡ማለት፡አረንጓዴ—ቢጫ—ቀይ፤ተራሮችና፡ሸለቆች፤ወንዞችና፡ሐይቆች፤ያገር፡ውበት፤የ፫ሺ፡ዘመን፡ነፃነት፤ታሪካችንና፡ንጉሣችን፡ጠረፋችን፡«አንድነታችን»፤ጥንታዊ፡ሃይማኖታችን——፤የነርሱ፡ኢትዮጵያ፡ይህቺ፡ናት፡፡ኢትዮጵያ፡ለም፡ሃገር፤ምድራዊ፡ገነት፤ገበሬውም፡ሆነ፡ሠራተኛው፡ምን፡ጐደለው?ዛሬ፡ሁሉም፡ሰው፡ለመሥራት፤ለመማር፤መማከርቱን፡ለመምረጥ፡ነፃ፡አይደለምን?ታዲያ፡የገበሬና፤የሠራተኛ፤ሬቮሉሽናዊ፡ለውጥ፡ምን፡አሰኘን፡ይላሉ፡፡ያሁኑን፡ሕብረተሰባዊ፡አቋም፡አበጥሮ፡ማየትና መኰነን፡ለነርሱ፡ሃገርን፡ማስደብ፡ነው፡፡የሕይወትን፡ትርጉምና፡የመደቦችን፡ትግል፡ያልተማረው፡ያገራችን፡ገበሬ፡ከነርሱ፡አብልጦ፡በቀላሉ፡ይረዳዋል፡፡ስለዚህ፡ከነርሱ፡ውስጥ፡በጣም፡ጥቂቶቹ፡ብቻ፡ሊማሩ፡ይችሉ፡ይሆናል፤

ርዕስ—አንቀጽ፤

## በአውሮፓ፡የኢ.ት፡ተማ፡ማ፡፫ኛ፡ጠ፡ጉባኤ፡—

እንደአውሮፓ፡አቆጣጠር፡ከነሐሴ፡፲፪—፲፰፡፲፱፻፷፰ዓ.ም፡በዛግሬብ፡ዩጎዝላቪያ፡የተደረገው፡በአ፡የኢ.ት፡ተ፡ማ፡ማ፡፫ኛ፡ጠቅላላ፡ጉባኤ፡ዘንድሮም፡አንዳንድ፡ትላልቅ፡ድሎችን፡ተቀዳጅቷል።ይጠበቁ፡ከነበሩት፡አሥራስድስት፡ማኅበራት፡ውስጥ፡ያሥራሦስቱ፡ማኅበራት፡ሐላፊዎች፡ወይም፡ወኪሎች፡ሲገኙ፡እንደዚሁም፡በማኅበሩ፡ታሪክ፡ውስጥ፡ለመጀመሪያ፡ጊዜ፡በሰሜን፡አሜሪካ፡ያሉ፡የትግል፡ጓዶቻችን፡አንድ፡መልክተኛ—ጓድ፡ሐጐስ፡ገ፡የሱስን—ልከው፡ነበር።

አድሃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡የማኅበሮቻችንን፡አንድነት፡ለማፍረስና፡ትግላችንን፡ለማድከም፡ወስዶት፡የነበረውን፡እርምጃ፡ሁሉ፡ስናስታውስ—ለምሳሌ፡በያገሩ፡የተማሪዎቹን፡መደጐሚያ፡በመቀነስ፡የፓስፖርት፡ችግሮችን፡እየፈጠሩ፡ተማሪዎች፡ከሉበት፡እንዳይንቀሳቀሱ፡ለማድረግ፡በመሞከር፡ስለማኅበሩ፡አመራር፡ከንቱና፡ሐሰተኛ፡ወሬዎችን፡በማስወራት፡ወዘተ፡—ያሥራሦስቱ፡ማኅበራት፡መገኘትና፡የጉባኤው፡መልካም፡ውጤት፡መስጠት፡እንደትልቅ፡ድል፡ሊቆጠር፡ይገባዋል።በፖለቲካው፡በድርጅቱና፡በቆራጥነቱ፡አንድነቱን፡አጠንክሮና፡በትግል፡እሳት፡ተፈትኖ፡የወጣ፡ማኅበር፡ሆኗል፡ለማለት፡ይቻላል።የጠላቶቹ፡ተንኮል፡አሁንም፡እንደገና፡ከመክሸፉም፡በላይ፡የማኅበሩን፡ጥንካሬ፡ጭምር፡አስከትሏል።

ነገር፡ግን፡የማኅበሩ፡ጥንካሬና፡ቆራጥነት፡በጨመረ፡ቁጥር፡የማኅበርተኞቹ፡የመንፈስ፡ንቃትና፡ዝግጁነት፡እየዳበረ፡በሄደ፡ቁጥር፡ያድሃሪ፡ጠላቶችም፡ተንኮል፡በዓይነትና፡በብዛት፡እየጨመረ፡ይሄዳል።የሕዝብን፡ወገን፡በመምረጥ፡ላዲስ፡ሕዝባዊት፡ኢትዮጵያ፡የሚታገል፡ሁሉ፡ድምጽ፡እንዲታፈን፡ለማድረግ፡አድሃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡በማንኛውም፡የተንኰል፡ዘዴ፡ከመጠቀም፡አይመለስም።አንዳንዴ፡በማስፈራሪያ፡አንዳንዴ፡በድለላ፡ይጠቀማል፤መንፈሰ—ደካሞችን፡በቀላሉ፡እንደሕፃን፡ያታልላቸዋል፤አድር—ባዮችን፡በቀጥታ፡ይገዛቸዋል፤በሰላዮቹና፡በቡችሎቹ፡በመጠቀም፡በወሬና፡በዛቻ፡ለመበታተን፡ይሞክራል።አድሃሪዎች፡እስከዕለተ—ፍጻሜያቸው፡ድረስ፡ይፍጨረጨራሉ፡እንጂ፡«በመልካም፡ፈቃዳቸው»፡ሥል



ጣንን፡ለሕዝብ፡አያስረክቡም፤ሕዝቡ፡የወደፊት፡ዕድሉን፡በፈለገው፡መንገድ፡እንዲቀይሰው፡አይፈልጉም፤ይህ፡መሠረታዊ፡ባሕሪያቸው፡ስለሆነ፡አድሃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡ከዚህ፡ሕግ፡ሊያመልጥ፡አይችልም።

ይህ፡ከሆነ፡ማኅበራችን፡ካለፈው፡ትግሉ፡ተገቢውን፡ትምህርት፡በመቅሰም፤ስህተቶችን፡በማረምና፡የጠላትን፡ተንኮል፡ነቅቶ፡እየተጠባበቁ፡በማክሸፍ፤ትግሉን፡ወደከፍተኛ፡ደረጃ፡ለማድረስ፡በታላቅ፡ትጋትና፡ጥንቃቄ፡ወደፊት፡መገስገስ፡ይኖርበታል።በዚህ፡መሠመር፡የጉባኤውን፡ዋና፡ዋና፡ውጤቶች፡መመዝገብ፤የነበሩትን፡ችግሮች፡ወይም፡ጉድለቶች፡መመልከትና፡ስለማኅበሩ፡የወደፊት፡እርምጃ፡ማሰብ፡ያስፈልጋል።

የማኅበሩን፡የወደፊት፡ግስጋሴ፡ሊያረጋግጥ፡የሚችለው፡የንቁ፡ማኅበርተኞች፡ትጋትና፡ቆራጥነት፡ነው።እነዚህ፡ትጉ፡ቆራጥና፡ባለሕሊና፡ማኅበርተኞች፡ያውሮፓውን፡ማኅበር፡የአባላት፡ዓይነት፡ከተመለከቱ፡በኋላ፡በርከት፡ያሉት፡ማኅበርተኞች፡በሪቮሉሽናዊ፡ሰንደቅ፡ዓላማ፡ሥር፡ሊሰለፉ፡የሚችሉበትን፡ዘዴ፡ሳይታክቱ፡መፈለግ፡አለባቸው።

እንግዲህ፡በያመቱ፡ጠቅላላ፡ጉባኤ፡ሲደረግ፡ከስብሰባው፡ላይ፡የሚገኙ፡ምን፡ዓይነት፡አባሎች፡ናቸው?

ከሚመጡት፡አባሎች፡ጥቂቶቹ፡በቀጥታ፡ከፊውዳላዊው፡ዓለም፡አብራክ፡የወጡ፤የፊውዳላዊ፡ርእዮተ—ዓለማቸውን፡ለመለወጥ፡ያልሞከሩ፡ወይም፡ሞክረው፡ያልቻሉ፤ከሕፃን፡አንጐላቸው፡ጋር፡እንዲጣበቅ፡ከተሰጣቸው፡አደንቋሪ፡ትምህርት፡ነፃ፡ለመውጣት፡ያልቻሉ፡ናቸው።ለነዚህ፡ሰዎች፡«ኢትዮጵያ»፡ማለት፡አረንጓዴ—ቢጫ—ቀይ፤ተራሮችና፡ሸለቆች፤ወንዞችና፡ሐይቆች፤ያገር፡ውበት፤የ፫ሺ፡ዘመን፡ነፃነት፤ታሪካችንና፡ንጉሣችን፤ጠረፋችን፤«አንድነታችን»፤ጥንታዊ፡ሃይማኖታችን——፤የነርሱ፡ኢትዮጵያ፡ይህቺ፡ናት።ኢትዮጵያ፡ለም፡ሃገር፤ምድራዊ፡ገነት፤ገበሬውም፡ሆነ፡ሠራተኛው፡ምን፡ጐደለው?ዛሬ፡ሁሉም፡ሰው፡ለመሥራት፤ለመማር፤መማከርቱን፡ለመምረጥ፡ነፃ፡አይደለምን?ታዲያ፡የገበሬና፤የሠራተኛ፤ሪቮሉሽናዊ፡ለውጥ፡ምን፡አሰኘን፡ይላሉ።ያሁኑን፡ሕብረተሰባዊ፡አቋም፡አበጥር፡ማየትና፡መኰንን፡ለነርሱ፡ሃገርን፡ማሰደብ፡ነው።የሕይወትን፡ትርጉምና፡የመደቦችን፡ትግል፡ያልተማረው፡ያገራችን፡ገበሬ፡ከነርሱ፡አብልጦ፡በቀላሉ፡ይረዳዋል።ስለዚህ፡ከነርሱ፡ውስጥ፡በጣም፡ጥቂቶቹ፡ብቻ፡ሊማሩ፡ይችሉ፡ይሆናል፤

የሚበልጡት፡ግን፡ተስፋ፡የሌላቸው፡አድሃሪውያን፡የፊውዳሉ፡አገዛዝ፡የወደፊት፡ቀኝ—አጅ፡ናቸው።

የነዚህ፡አድሃሪውያን፡ቀጥታ፡ተቃራኒ፡የሆኑ፡ቁጥራቸው፡ያነሰ በላብ—አደሩ፡ሕዝብ፡ርእዮተ—ዓለም፡ላይ፡የተመሠረቱ፡ከፍተኛ፡የመንፈስ፡ንቃት፡ያላቸው፡ቆራጥ፡ኢትዮጵያውያን፡አሉ። ለነዚህ፡«ኢትዮጵያ»፡ማለት፡የማይጨበጥ፡የሕያንነት፡ወራት፡ቅዠት፡አይደለም፤ከሁሉ፡አስቀድሞ፡ገበሬውና፡ሠራተኛው፡ነው። ዘጠና፡በመቶ፡የሚሆነው፡ሠርቶ—አደሩ፡ሕዝብ፡ድሀ፤መሐይም፤በሽተኛና፡ተጨቋኝ፡የሆነው፡ከላዩ፡ላይ፡ሀብታም፤አዋቂ፤ጤነኛና፡ጨቋኝ፡የሆኑ፡መደብ፡ስላለበት፡መሆኑን፡አውቀውታል። የሕብረተሰብን፡መሠረታዊ፡አስተዳደግ፡ሕጎች፡ስለተገነዘቡ፡እንደአድሃሪውያን፡በጠባብ፡ብሔራዊ፡ስሜት(ናሽናሊዝም)፡አይታለሉም። በኢትዮጵያ፡ጨቋኝና፡ተጨቋኝ፡መደቦች፡እንዳሉ፡ሁሉ፡በዓለምም፡ጨቋኝና፡ተጨቋኝ፡ሃገሮች፡እንዳሉ፡ያውቃሉ። በኢትዮጵያም፡ሆነ፡በዓለም፡ጨቋኞች፡ወደፊት፡ከጥፋት፡እንደማያመልጡ፡የታሪክ፡ሕግ፡እንደሆነና፡ይህንን፡ቀን፡ለማፋጠን፡በመደብ፡ትግል፡እሳት፡ገብቶ፤ግለ—ሰበኝነትን፡ጥሎና፡መሥዋዕትነትን፡ተቀብሎ፡ከላብ—አደሩ፡ሕዝብ፡ጋር፡መሰለፍ፡ቀዳማዊ፡ተግባራቸው፡መሆኑን፡አምነው፡የሕይወታቸው፡ዓላማ፡አድርገውታል።

በነዚህ፡በሁለት፡የአባል፡ዓይነቶች፡መካከል፡የሚገኙት፡በቁጥራቸው፡ከሁለቱም፡በጣም፡ይበልጣሉ። እነዚህ፡የኢትዮጵያን፡ሕብረተሰብዊ፡ሁኔታና፡የዓለምንም፡ታሪክ፡በመጠኑ፡ያውቃሉ። የጠለቀ፡ዕውቀት፡አይደለም። በስሜታቸው፡የሚሰለፉት፡ከግንባር—ቀደሙ፡ክፍል፡ጋር፡ስለሆነ፡ዕውቀታቸውን፤መንፈሳቸውንና፡በትግል፡ተሳታፊነታቸውን፡ለማስፋት፤ለመማር፤ሬቮሉሽናዊ፡አስተያየትን፡ከኑሮአቸው፡ጋር፡ለማዋሀድ፡ይጓጓሉ፤ዝግጁም፡ናቸው። ዋናው፡ችግራቸው፡የሬቮሉሽናዊ፡የቀለም፡ትምህርት(ቲዎሪ)፡ጉድለት፡ነው። በመጽሔቶቻችን፤በሌሎችም፡ሬቮሉሽናዊ፡ጽሑፎችና፡ጋዜጦች፡ቢገለገሉ፡ይህንን፡ጉድለት፡በመጠኑ፡ሊያስወግዱት፡ይችላሉ።

ከአድሃሪው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡በየጊዜው፡የሚላኩትን ሰላዮችና፡በጥባጮች(ፕሮቮካተሮች)፡ሳንቆጥር—እፍኝ፡አይሞሉምና—በያመቱ፡በሚደረገው፡ጠቅላላ፡ጉባዔ፡የሚገኙት፡አባላት፡ዓይነት፡ይህ፡ስለሆነ፡የሚደረገው፡ክርክርም፡ሁለት፡መልክ፡ይዞ፡ይገኛል። የመጀመሪያው፡



መልኩ፡ይበልጡ፡ግንባርተኛ፡አንድነት፡ሆኖ፡የሚያንቀሳቅሰው፡ትምህርታዊ፡ክርክር፡ነው፤ሁለተኛው፡ደግሞ፡በጥቂቶቹ፡አድሃሪዎችና፡በወደፊት፡ተራማጅ፡መካከል፡የሚደረገው፡የርእዮተ—ዓለም(ኢዲዮሎጅ)፡ግጭት ነው። (በነዚህ፡በሁለት፡ዓይነት፡ትግሎች፡መካከል፡መካኒካዊ፡ልዩነት፡ለማድረግ፡እንደማይቻል፡መዘንጋት፡የለብንም፤ለትንተና፡እንዲመች፡ጣምራ፡መልክ፡ተሰጣቸው፡እንጂ፡ዘር፡ዘር፡ማንኛውም፡የጉባዔ፡ክርክር፡የሁለት፤አንዳንዴም፡የሦስት፤ኢዲዎሎጅዎች፡ግጭት፡መሆኑን፡አንርሳ።)

በ፳ኛው፡ጉባዔያችን፡ላይ፡የተደረገውን፡የኢኮኖሚና፡የሕብረተሰባዊ፡አቋም፡ትንተና፡እንደትምህርታዊ፡ትልም፡ለመውሰድ፡ይቻላል። «ሕዝባዊ፡ንቅናቄ፡በኢትዮጵያ»፡የሚለው፡አርእስት፡ግን፡አድሃሪዎችንና፡ተራማጆችን፡በቀጥታ፡አጋጭቷቸዋል። የመጀመሪያውን፡አርእስት፡ዘርዝረን፡ባጠናንበት፡ጊዜ፡ከላይ፡የጠቀስናቸውን፡የአባላት፡ዓይነቶች፡ለማየት፡ተችሏል። ዋናው፡ክፍል፤ማለት፡አእምሮውን፡ከፍቶ፡ለመማር፡የተዘጋጀው ክፍል፡ያቀርባቸው፡ከነበሩት፡ዓይነተኛ፡ጥያቄዎች፡አንዱ፡«ቡርዡዋ፡ማለት ምን፡ማለት፡ነው?»የሚለው፡ሲሆን፤አድሃሪዊ፡አስተያየት፡ያለው፡ክፍል፡ደግሞ፡ስለዚሁ፡መደብ፡«አባቶቻችን፡ናቸው፡እኮ!»ይል፡ነበር። «ዝምባብዌ፡ደግሞ፡የት፡ነው?»የሚለው፡ጥያቄና፡«አረቦችን፡ለምን፡እንደግፋለን?» የሚለው፡እንደሰማይና፡ምድር፡የተራራቁ፡ጥያቄዎች፡ናቸው። የመጀመሪያው፡የሬቮሉሽናዊውን፡ዓለም፡ትግል፡አለመከታተሉን፡ጋዜጦችን፡በማንበብ ስለሕዝቦች፡እንቅስቃሴ፡አለማወቅንበጭሩ፡የሬቮሉሽናዊ፡ዜናጉድለትን ያሳያል፤ሁለተኛው፡ግን፡ጠለቅ፡ያለ፡ኢዲዮሎጂያዊ፡አቋምን፡ይገልጻል። «አረቦችን፡አገራችን፡እናውቃቸዉ፡የለምን? በእስላሞች፡ተከበናል! ንጉሣችን፡ሁለት፡መቶ፡ሀያ፡አምስተኛዉ፡የሰለሞን፡ዲናስቲ፡ነዉ፤እሥራኤል፡የኛ፡ወገን፡ናት!»የሚሉትን፡አድሃሪ፡አስተያየቶች፡አዝሏል። እያንዳንዱ፡ሰዉ፡አሳቡን፡ለመስጠት፡ሊሳኑን፡በከፈተ፡ቁጥር፡የሚያወጣቸዉ፡ቃላት፡የመደቡ፡፣ርእዮተ—ዓለም፡ማህተም፡ይዘዉ፡ይወጣሉ። ያገራችን፡ሕዝባዊ፡እንቅስቃሴዎች፡በተወሱ፡ቁጥር፡«አንድነታችንስ?»እያሉ፡ያላንዳች፡ምርመራ፡የገበሬዉንና፡የሠራተኛዉን፡ትግል፡መቃወም፤«ማንኛዉም፡ክፍለ—አገር፡ከተነካ፡በጦር፡ኃይል፡መደምሰስ፡አለበት፡»የሚል፡ፋሺስታዊ፡አሳብ፡ደፍሮ፡መናገር፤ከድሃሪዉ፡የኢትዮጵያ፡አገዛዝ፡ጋር፡በመሠለፍ፡የሠርቶ—አ

ደሩ፡ሕዝብ፡ጠላት፡መሆን፡ነው።

አሁን፡ባለንበት፡ጊዜ፡አድሃሪው፡የኢትዮጵያ፡አገዛዝ፡በሁሉም፡ወገን፡ተወጥሮ፡በመያዙ፡በችግር፡ላይ፡ችግር፡ደርሶበታል። በባሌ፤በቦረና በኤርትራ፡በሚደረጉት፡ሕዝባዊ፡ትግሎች፡ላይ፡አሁን፡ደግሞ፡የጐጃም፡ሕዝብ፡ትግል፡ተጨምሯል። በቆራጥ፡መንፈስ፡የሠርቶ—አደሩን፡ወገን፡የመረጡት፡የኢትዮጵያ፡ዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፡አሁን፡በቅርቡ፡እንደገና፡ትግላቸውን፡አፋፍመው፡አድሃሪውን፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡አንቀው፡በመያዝ፡አንዳንድ፡ድሎችን፡ከማግኘታቸውም፡በላይ፡በጠቅላላው፡የተጨቆነውን፤የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡ሬቮሉሽናዊ፡የመንፈስ፡ንቃት፡ከፍ፡ካለ፡ደረጃ፡ላይ፡አድርሰውታል። በዓለም፡በኩል፡የሆነ፡እንደሆነ፡ኢምፔሪያሊስት፡አገሮች፡በታላቅ፡የኢኮኖሚ፡ችግር (ክራይሲስ)፡ላይ፡ከመውደቃቸውም፡በላይ፡ሬቮሉሽናዊ፡የዓለም፡ሕዝቦች፡ለብሄራዊ፡ነፃነትና፡ለዴሞክራሲ፤ለሶሻሊዝምና ለሰላም፡የሚያደርጉት፡ትጋድሎ፡የኢምፔሪያሊስቶችን፡ኃይል፡በጣም፡አድክሞታል።

በዚህ፡ምክንያት፡ዛሬ፡ባገራችን፡ወጣቶች፡ዘንድ፡ለሳይንሳዊ፡ዕውቀትና፡መፍትሔ፡ትልቅ፡ጉጉት፡አለ። ላገራችን፡ፕሮብሌሞች፡መፍትሔ ይሆናሉ፡የሚባሉትን፡መንገዶች፡ንቁ፡ኢትዮጵያዊ፡ሁሉ፡በመፈለግና፡በማሰላሰል፡ላይ፡ነው። በዚህ፡ሁናቴ፡የማኅበራችን፡ዋና፡ተግባር፤ትምህርታዊ፡ክርክርን፡በማስፋፋትና፡የኢዲዮሎጂ፡ትግልን፡በማድረግ፡ዘጠና፡በመቶውን አባል፡ባንድ፡ዓላማ፡ሥር፡ለማሰለፍ፡መሆን፡አለበት። በተጨበጠ፡መንገድ፡ሲታሰብ፡ለነዚህ፡ትግሎች፡ማኅበሩ፤አንደኛ፤መጽሔቶቻችን፡በሰፊው፡እንዲነበቡና፡እንዲሰራጩ፤ሁለተኛ፤በየቦታው፡የተቋቋሙት፡የሕብረተሰብ፡ኢትዮጵያውቅና፡ኮሚቴዎች፡እርግጠኛ፡የመማሪያና፡የመንፈስ፡ማንቂያ፡ቦታ፡እንዲሆኑ፡መጣጣር፡አለበት። ማኅበራችን፡ግንባሩን፡እየጨመረ፡ከሄደ፤እያንዳንዱ፡ንቁ፡አባል፡ትጋቱን፡ከጨመረና፡የተቻለውን፡ሁሉ፡ድጋፍ፡ከሰጠ፡ገና፡ወደፊት፡ብዙዎችን፡ደግሞ፡ከሁኑ፡የበለጡ፡ድሎችን፡እንደሚቀዳጅ፡አይጠረጠርም።

**የኢትዮጵያ፡ላብ—አደር፡ሕዝብ፡ያሸንፋል!**



## ከአበበ፡ቢቂላ፡እስከ፡ማሞ፡ወልዴ።

ከአድማሱ

ምስኪን፡አበበ፡ቢቂላ፤የሮማው፡የቶኪዮው፡ጀግና። ደግሞም፡የሚክሲኮው፡አርአያ። አራት፡ዓመት፡ይረሱህና፡እንደተቀመጠ፡ዕቃ፤እንደገና፡በሌ፡ናሩ፡ዋ፤ለባንዲራህ፤ለንጉሡ፡ነገሥት፡ይሉሀል። ታመሀል? ኪዱ፤ አሳክሙት፤ጀርመን፡አገር፡ይባላል። ደከምክ፡አትልም፤እሺ፡ትላለህ፤እምቢ፡ብትል፡የት፡ልትገባ? ሞከርከ፤አልበዘንክም። አይዞህ፤ፈታቸውን፡እንዳያጠቁሩ፡ብህ፡ሌላ፡አበበ፡ቢቂላ፡ተክተሀል።

አቤ፤እኛ፡ግን፡አንረሳህም። የሮማውን፡የቶኪዮውን፡ደግሞም የሚክሲኩን። አንተ፡ነህ፤ለመጀመሪያው፡ጊዜ፡የነገርከን፡ትልቁን፡አሳብ፤ኢትዮጵያም፡ይቻላል፤ለሞከረ፤ለበረታ፡ከአቅም፡በላይ፡የሚመስለው፡ይቻላል — ስትል።

ለሰው፡ልጅ፡ዛሬ፡ሩቅ፡የሚመስለው፤ለብዙዎች፡የማይታየው ኢትዮጵያም፡ውስጥ፡ይቻላል።

---

## ያገር፡ቤት፡ወሬ።

የመምህራን፡ማኅበር፡በኀሐሴ፡መጨረሻ፡ስብሰባ፡አድርጐ፡ነበር ፲፩፡ጠቅላይ፡ግዛት፡እንደራሴ፡ልኳል። ማኅበሩ፡ገና፡አልጠናም። አባሎች፡ትንሽ፡ናቸው። ከ፲፩፳ (፱፳፡ኢትዮጵያውያን) አስተማሪዎች፡የተመዘገቡት፡አባሎች፡፳፡የሚገቡ፡አይመስሉም። አንዱ፡ምክንያት፡በየጊዜው፡የሚመርጧቸው፡መሪዎች፡ለተቋሚዎቻቸው፡በመርዳት፤መቶም፡እነሱን፡በመፍራት፤የአስተማሪዎችን፡ድምፅ፡በደንብ፡አላሰሙም። አስተማሪዎችም፡ምን፡ሠራችሁልን? አባል፡መሆን፡ዋጋ፡የለውም፤የሚል፡ድምፅ፡ያሰማሉ። የተመረጡት፡መሪዎች፤ፍጹም፤አስተማሪዎች፡ገንዘብ፡አይከፍሉም፤ይህን፡አድርጉ፡ስንላቸው፡አይታዘዙንምና፤እኛ፡ተጋፍጠን፡ማን፡ያድነናል? የሚል ነው፡ሀሳባቸው። ስለዚህ፡በየገጠሩ፡ያሉት፡አስተማሪዎች፡በደንብ፡ሊደረጁ አልቻሉም። የአዲስ፡አበባው፡ግን፤የጠነከረ፡ሕብረት፡አላቸው። ማኅበሩ፡ጥ

ሩ፡አመራርና፡ብዙ፡መቶ፡አባል፡አለው። እ፡አ፡ሕብረት፡ጠንከር፡ያለ፡ስላለ፡በ
ሚያገኘው፡ወር፡ትምህርት፡ግቆማቸው፡(ለጅ፡ቀን፡)የታወቀ፡ነው። ምክንያቱ
ም፡ደሞዝ፡ነው።«እስኬል» ይሉታል።«እስኬል»የትምህርት፡ደረጃ፡ብቻ፡
ይመለከትና፡ደሞዝ፡ይመድባል።« ቲቸር፡ትሬይኒንግ »የጨረሰ፡፪፻፴፡ብር፡
ድር፡፪፻፡ነበር። ግን፡የዛሬ፡አሥር፡ዓመት፡የጨረሰ፡በየጊዜው፡ጭማሪ፡አግኝ
ቶ፡ዛሬ፡፪፻፺፱፡ደርሶ፡እንደሆነ፡በ፲፱፻፷፩፡የጨረሰው፡እኩል፡ያገኛል። ሁለቱ
ም፡፪፻፶፡ብር። ፩፡ብር፡ጭማሪ፡ብቻ፡አለው። የብዙ፡ዓመት፡አገልግሎት፡ያላቸ
ው፡የትምህርት፡ቤት፡ወረቀት፡ከሌላቸው፡ጭማሪ፡የላቸውም። አገልግሎት
ዋጋ፡የለውም ይ?ነው፡የሚሉት።

ይህን፡በመቃወም፡እ፡አ፡አበበች፡ሥራ፡አቆሙ። ጃንሆይ፡ዘንድም፡
ደርሰው፡ጉዳዩ፡እንደገና፡ይጠና፡ተብሎላቸውና፡ሥራ፡ጀመሩ። ዋናው፡የኢ
ትዮጵያ፡መምህራን፡ማኅበር፡መሪዎች፡ግን፡ከማህበራቸው፡ለጊዜው፡አሶጧ
ቸው። ያለጉባዔ።

በነሐሴ፡ስብሰባ፡ላይ፡ግማሽ፡ጠቅላይ፡ግዛት፡አዲስ፡አበባን፡ተቃ
ወመ፤ ግን፡ማኅበራቸው፡መወገዱን፡አልተቀበሉትም። ጥርጣሬው —አዲስ
አበቦች፡የገጠርን፡ሊጠቀሙበት፡ነው፤ እነሱ፡ሁሉ፡በጃቸው፤ ሁሉ፡በደጃቸ
ው፡ነው፤ ከዚህም፡በላይ፤ ደግሞ፡ገጠርን፡ሊበልጡ፡ይፈልጋሉ — እየተባለ፡
በመሐላቸው፡ማሻከሪያ፡ይነዛል። ገጠሮችም፡የሚመርጡት፡ዲሬክተሮችና
አስተዳዳሪዎች፡ይበዙበት፡ስለነበር፡እነርሱ፡የመምህራንን፡ድምፅ፡በስብሰባ
ው፡ላይ፤ በሙሉ፡ሊገልጡ፡አልቻሉም። ከዚህም፡የተነሳ፡ከአዲስ፡አበባው፡
ጋር፡ይጋጩ፡ነበር። እ፡አ፡አክሊሉ፡ሀብቴ፡እንዳይመረጥ፡ሲጥር፡ገጠር፡ደግፎ
ት፡ተመረጠ። ግን ሌላ፡ተወዳዳሪ፡እን ዳይቀርብ፡ዘጉ።«ገባህ፤ አንተው፡ማኅበ
ሩን፡ያገለግን፤ ሌላ፡የመጣ፡እንደሆነ፡ከኛ፡ያርቅብናል»ያሉት፡ኃይሎች፡አሉ፤
ብለው፡ያማሉ።

ገጠር፡ገና፡ብዙ፡ችግር፡አለበት። ገጠር፡በሙሉ(መምህራኑ፡ተ
ማሪው፡ገበሬው፡ወዘተ፡)ገና፡ታዛዥ፡ነው። የሎሌነትና፡የጌታን፡ግንኙነት፤ የገ
ዢና፡የተገዢን፡ባህል፡ገና፡እንደ፡«ዕድል፡ደረጃ»፡ይቀበሉታል። ይህ፡ግን
ኙነት፡ሳይነካ፡ትንሽ፡ለኑሮአቸው፡መሻሻል፡ከላይ፡እንዲደረግላቸው፤ ይለ
ማመጣሉ።«መብታቸውን፡ይለምናሉ»፡ብሎ፡ማኅበሩ፡አወገዛቸው። ሲገዛ
፤ ሲጨቆን፡የኖረ፡ሕዝብ፡ፍርሃትን፡በጊዜ፡ብዛት፡ከባሕርዩ፡አዋህዶ፡ጭቆና
ውን፡ለማስወገድ፤ ይህ፡ፍርሃት፡እንቅፋት፡ይሆንዋል። ጭቆናውም፡ይቀጥላ
ል።



በተማሪዎችም፡ዘንድ፡ተመሳሳይ፡ሁናቴ፡ይታያል። ከገጠር፡የ
መጣ፤ የሎሌ፡ልጅ፡ፈሪ፡ነው፤ ታዛዥም፡ነው። የበላዮችን፡መጋፋት፡ግብረገብ
ማጣት፡ይሆንበታል። መብቱን፡ይለምናል። የከተማው፡ወጣት፡ግን፡የ«በላ
ይ፡ምንድነው?»የሚል፡ጥያቄ፡ከማቅረቡ፡በላ ይ፤ የሎሌነትና፡የጌታን፡ግንኙነ
ት፡አለመቀበሉን፡ኃይል፡በመጠቀም፡አሳይቷል። ለጥ፡ብሎ፡እጅ፡መንሳትን
በተፈለገ፡ጊዜ፡መታዘዝን፤ ለአተማሪዎች፡መርበድበድን፡ትቶታል። ሥልጣ
ንን፡ማክበርና፡ማወደስ፡በከተማው፡ወጣት፡ዘንድ፡በኃይል፡ተቀንሷል። ገጠ
ር፡እዚህ፡ሕሊና፡ደረጃ፡አልደረሰም።

ከገጠር፡ወደዚህ፡መቃወም፡የደረሰ፡የጉጂም፡ገበሬ፡ነው፡ይባላ
ል። አዲሱን፡የታክስ፡ሥርዓት፡የወደደው፡ሰው፡ጨርሶ፡የለም።«ማለት፡ከሕ
ግ፡አመንጪዎች፡በቀር።»ከዳር፡እስከዳር፡ገጠር፡በልቡ፡«አየጉድ» ይል፡ይ
መስላል። ጉጂም፡ግን፡(ጉንደርም፡እንጎራጉር፡ነበር፡ይባላል)ተቃወመ። ለ
ምን?

የአዲሱን፡ታክስ፡አሰባሰብ፡ለማቃለል፡የገበሬውን፡መሬት፡መ
መተርና፡መለካት፡አስፈላጊ፡የሆነ፡ይመስለኛል። ባህላዊው፡የመሬት፡ይዞታ
ድብልቅልቅ፡ስላለ፡ለግብር፡ገማችና፡ሰብሳቢ፤ ያስቸግራል፡ይመስላል። ጉጂዎች
የመሬትን፡መመተር፡የተከላከለው፡ቀላድ፡ምን፤ እንደሆነ፤ መሬት፡ከተመተ
ረና፡በግል፡ሰው፡ከተገበረበት፡ጥንታዊውን፡መብት፡እንደ፡ሚያፈርስበት፡ስ
ለሚያውቅ፡ነው። ይህ፡ከፈረሰ፡የገበሬው፡ሕይወት፤ ዋስትና፡ይጠፋል። ጥን
ታዊው፡ይዞት፡በመጠኑ፡የሕይወት፡ዋስትና፡አለው። ማለት፤ መሬት፡የግል፡
አይደለም፤ የቤተሰብ፤ የጋራ፡ነው። አይሸጥም፤ አይለወጥም። የትም፡ዞር፤ የት
ም፡ሄዶ፤ ቢቸገረው፤ ዘምድናውን፡ቆጥር፡ሲመለስ፡የሚያርሰው፡መሬት፡ከ
ቤተሰብ፡የማግኘት፡መብት፡አለው።

በአሁኑ፤ ሥርዓት፡ግን፡መሬት፡ተመትሮ፡በግል፡ሰው፡ከተገበረ
በት፡የግል፡ሰው፡ሀብት፡ሊሆን፡ነው። መሬት፡የኔ፡ነው፡ብሎ፡መናገሪያ፡ሊያሳጣ
ው፡ይችላል። መሬት፡በትንሽ፡ሰዎች፡እጅ፡ይገባል። ይህ፡በሌላው፡ጠቅላይ፡ግ
ዛት፡ላይ፡ችግር፡ማድረሱ፡ከተገነዘቡት፡ይመስላል። ትናንሽ፡የሆኑ፡ሁሉ፡ያው
ቃሉና። ስለዚህ፡ጉጂም፡በሙሉም፡ባይሆን፡ስለተቃወመ፡መንግሥቱ፡ጦር፤
ኃይል፡ላከ። የወረዳ፡ገዢዎችና፡የፓርላማ፡ምርጦች፡በሰውነታቸው፡ወይ፤
በሀብታቸው፡ላይ፡አደጋ፡ደርሶባቸዋል፤ ተብሎ፡በሰፊው፡ይወራል። ከመንግ

ዞትን፡አሳፋሪና፡ምስኪን፡ሀብት፡ተቆራኝተው፡እንዲሁ፡በየጠላና፡በየቡና፡ቤቱ፡«ለሀገርና፡ለወገን»፡ተቆርቋሪነታቸውን፡እየነዙ፡መስለው፡ይኖራሉ። እነዚህ፤ቆርጠው፡ስላልተነሱ፤ታሪክን፡በሚገባ፡ስላልተመራመሩ፤ታግሎ፡ለመጣል፤ተዋግቶ፡ለማሸነፍ፡የሚቻል፡አይመስላቸውም። ይህ፡አስተያየታቸው፡ዋጋቢስ፡የመኝደር፡ወሬ፡ብቻ፡መሆኑን፡ታሪክ፡ይመሰክርባቸዋል።

አዲሱ፡መኳንንት፤በሌላ፡በኩል፡ስንመለከተው፡ደግሞ፤እንደ አርጌው፡ሁሉ፡ዕውነተኛ፡የመደብ፡ጥቅሙን፡የሚከባከብ፡ሆኖ፡እናገኘዋለን፤ይኸውም፡የሌሎችን—የሠራተኛውንና፡የገበሬውን—የሥራ፡ፍሬ፡የመበዝበዝ፡ጠባይ፡ነው። ከከፍተኛው፡መደብ፡ጋር፡ጋብቻንና፡ክርስትናን፡በመሳሰሉ፡የዝምድና፡አረጐች፡በመተሳሰር፤እንዲሁም፡በሹመትና፡በማእርግ፡መቀዳጀት፡በመደለል፡የበሰበሰው፡ማኅበራዊ፡አቋምና፡የሥርዓቱ፤ደጋፊ፤የጥቅሙም፡ተካፋይ፡ሆኗል። እዚህ፡ላይ፡በተለይ፡የኦፖርቹኒስቶችን—ያድር፡ባይንና፡የመስሎ፡አደር፡አዲስ፡መኳንንትን—አሳሳች፡ባህርይና፡ሥራ፡ማስታወስ፡ያስፈልጋል።

አርጌው፡የመኳንንት፡ማኅበር፤የተበዘበዘውና፡የተጨቆነው፡ሕዝብ፡ነፃነቱን፡ለማግኘት፡የሚያደርገው፡ትግል፡ከጊዜ፡ወደ፡ጊዜ፡እየጠነከረ፡መሄዱን፤ስለተመለከተ፤የኸን፡አደጋ፡ለማቆም፡የጥንቱ፡ዘዴ፡ብቻውን፡በቂ፡እንዳልሆነ፡ስለተረዳ፤አዲስ፡ደም፡እየሠለጠነ፡ወደ፡ራሱ፡በማስገባት፡ሕይወቱን፡ለማርዘም፡ይጥራል። አዋቂ፡ነኝ፡ባዩ፡አዲሱ፡ቢሮክራት፡የበሰበሰውን፡የመኳንንትና፡የበላይ፡ዘር፡ተረት፡ተቀብሎ፡የሚጣልለትን፡የገንዘብ፡ጉርሻ፡የሚታዘዝለትን፡ደረጃና፡ሹመት፡ሚግ፡በመላስ፡እየተቀበለ፡በልዩ፡ልዩ፡መስመሮች፡የመጨቆኛ፡መሣሪያውን፡ቅልጥፍ ፡ለማሻሻል፡ይፍጨረጨራል። ይህ፡አዲስ፡ፍጡር፡ለአሳፋሪ፡ሙያው፡የሚሰጠው፡ምክንያት፡ማለቂያ፡የለውም። የታሪክ(የትኛውን፡ታሪክ፡ይሆን?)፤የልማድ፡መከበር፡አንዱ፡ነው። ወይም፡እርግጥ፡ያገራችን፤የሕዝባችን፡ሁኔታ፡ያሳዝናል፤ግን፡የኃይል፡መንገድ፡ጨርሶ፡ስህተት፡ነው፤(ለውጥ፤መሻሻል፡ያለኃይሎች፡ትግል፡ይመጣ፡ይመስል)፤እርግጥ፡ለውጥ፡ያስፈልጋል፤ብቻ፡ምን፡ሰው፡አለ?(እኔ፤ልሥራ፡እኔ፡ልጀምር፡ማለቱ፡ከኦፖርቹኒስቶች፡ጠባይ፡ዉጭ፡ነው።)ሕዝቡ፡አልነቃም(ድህዉ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በየጊዜዉና፡በየስፍራዉ—ባሁኑም፡ወቅት፡በባሌ፤በበረናበኤሪትራ፤በጎጃም—የጭቆናዉን፡አስተዳደር፡ሲታገል፡



ኦመጸኛ፡ወንጀለኛ፡በመባል፡የሚፈጸምበትን፡በደል፡ዓይኑም፡እንደመንፈሉ፡የሸገተው፡ዘመናዊ፡መኳንንት፡አይመለከተውም)። የኢትዮጵያ፡ላብአደር፡ሕዝብ፡ሀብትና፡ሶሻል፡ሁኔታው፡ግልጽ፡ነው፤ድህነትና፡ስቃይ፤ብዝበዛና፡ጭቆና፡ያጠቃው፡መንጋ፡ነው። ይህ፡ትልቅ፡የሬቮሉሽን፡ምክንያት(ረመጥ)፡መሆኑን፡መገንዘብ፡ያሻል።

ከጥንት፡ጀምሮ፡ሲያያዝ፡የመጣው፡የገጋርና፡የተገጋር፤የሠራተኛና፡ያሠሪ፤የጌታና፡የሎሌ፤የገባሪና፡ያስገባሪ፡ሥርዓት፡በታሪካዊ፡ኃይሎች፡ምክንያት፡እጅግ፡በተዳከመበት፡ባሁኑ፡ወቅት፡አዲሱ፡መኳንንት፡የሚፈጽመው፡ተግባር፡የሕዝብ፡ጠላትነቱን፡በጉልህ፡ያሳያል። በተለይም፡ከወሰኑ፡ላይ፡ተቀምጦ፡የራሱን፡ጥቅም፡እያሳደደ፤አሳቢ፡በመምሰል፤የነፋሱ፡አቅጣጫ፡እስኪለይ፡የሚጠብቀው፤ይህ፡ወላዋይና፡አጭበርባሪ፡መኳንንት፤ዛሬም፡ሆነ፡ኋላ፡ምንም፡የማይጠቅም፡ከመሆኑም፡በላይ፡አደገኛ፡ስለሆነ፡ወደፊት፡ተራማጅ፡ኃይል፡ከሁኑ፡ጀምሮ፡ከተቆራኘው፡አርጌ፡ሥርዓት፡ጋር፡ባንድ፡ሬት፡የሚታገለው፡ነው።

ይኸን፡አዲስ፡ደም፡የተሰራጨበትን፡አርጌ፡ሥርዓት፡ከስሩ፡ነቅሎ፡ለመጣል፡የኢትዮጵያ፡ሠራተኛና፡ገበሬ፡አንድነቱን፡ማጠንከር፡አለበት። የተጨቆነውን፡ሕዝብ፡ለመለያየትና፡አንድነቱን፡ለማድከም፡ብዙ፡የመደለያ፡ሙከራዎች፡ይደረጋሉ። ሆኖም፡የኢትዮጵያ፡ሠራተኛና፡ገበሬ፡የኑሮ፡ሁኔታ፡በዚህ፡ዓይነቱ፡የታይታ፡ሙከራ፡አንዲት፡ቅንጣት፡እንኳን፡ሊለወጥ፡ስላልቻለ፤ስለማይችል፡የጨቋኙ፡መደብ፡ጥረት፡ሁሉ፡ከንቱ፡ነው።

ለጤናው፡መጠበቂያ፤ለልጁ፡ማስተማሪያ፤ለኑሮው፡ማሻሻያ፡ሊውል፡የሚገባውን፡የሥራውን፡ፍሬ፤እግዚአብሔር፡መርጦናል፡እያሉ፡በመስበክ፤ለግል፡ትፍስህትና፡ክብር፡መላውን፡ዓለም፡በመዞርና፡እንግዳ፡በመቀበል፡ይፈነጩበታል። እንግሊዛዊው፡ሚል፡እንዳለው፡«ለራስ፡ጥቅም፡በማሰብ፡ሰዎችን፤የማይጎረብጡ፡መሣሪያዎች፡ይሆኑ፡ዘንድ፤ድንኩ፡የሚያደርግ፡መንግሥት፡በትንንሽ፡ሰዎች፡ትልቅ፡ሥራ፡ለማከናወን፡እንደማይቻል፡መገንዘብ፡ይገባዋል)። እነዚህ፡ያሁኑ፡ሥርዓት፡ድንኩ፡መሪዎች፡ባይገነዘቡት፡ነው፡እንጅ፡ዕውነተኛ፡ትልቅነት፡የሚገኘው፡ወገንን፡በማሳደግ፡ነው።

ድህው፡ገበሬና፡ሠራተኛ፡በመንግሥታዊ፡ኃይል፡ስለተጨቆኑ(ለጊዜው)ሊተባበር፡ባለመቻሉ፡የመከራው፡ድምጽ፡ተሸካሚዎች(ተቋቋ

ሥት። ጦር፡ ጋርም፡ በመጠኑም፡ ቢሆን፡ ግጭት፡ ተደርጓል፡ ይባላል። መጠኑን ና፡ ዓይነቱን፡ ለማወቅ፡ ያስቸግራል። ጉጃሞችም፡ «የፈለጋችሁትን፡ ግብር፡ ጠይቁን፤ ግን፡ መሬታችንን፡ አይለካ። አገረ ገዡው፡ ፅንቁ፡ ሥላሴ፡ ይወሰድልን» አሉ፡ ይባላል። ለጊዜው፡ አገረ፡ ገዢው፡ ተነሳ። ግብርም፡ በዱር፡ እንጅ፡ ባዲሱ፡ እንዳይከፍል፡ ለጊዜው፡ ተተውታል። ፅንቁ፡ ሥላሴ፡ ጅግ፡ ከፋ፡ ተሾመ። ጉጃም ውስጥ፡ ብዙ፡ ይዘፈናል። ይህ፡ አንዱ፡ ነው።

—ጉንደር፡ ስጋ
—ሸዋ፡ ስጋ
—ትግሬም፡ ስጋ፡ ወዘተ፡
—ጉጃምን፡ አሸረው
—ከፋ፡ ከሱ፡ ጠጣ።

ከፋም፡ መስፍን፡ ዕለሸን፡ ያውቅ፡ ነበር፤ ና፡ ሌላ፡ መስፍን፡ መጣብን፡ የሚል፡ ስሜት፡ አሳይቷል፡ ይባላል። አዲሱ፡ ሹም፡ አይምጣብን፡ ብለው፡ አቤቱታ፡ አቅርበዋል። ሠላማዊ፡ ሠልፍም፡ አደረጉ፡ ይባላል። «እኛ፡ ጋሎች፡ ደንቆሮዎች፡ ናቸው» ብላችሁ፡ ነው፡ ጉጃም፡ ያባረረው፡ ኸምትልኩልን? ይላሉ፡ አሉ። «ራስ፡ መስፍን፡ መሬታችንን፡ በግድ፡ ቀማን» ብለው፡ በየመንገዱ፤ ያወራሉ። አሁን፡ ያን፡ መሳይ፡ ሰው፡ መጣ፡ የሚል፡ ፍርሃት፡ ይመስላል፤ (ራስ፡ መስፍን፡ ሞቷል፡ ብሎ፡ የምኞት፡ ወሬ፡ ነዝቶም፡ ነበር።) ግን፡ በየሁኔታው፡ የሚታየው፤ በመሠረቱ፤ የሥልጣን፡ መቃወም፡ አይመስልም። የገዢ፡ ና፡ የሎሌነት፡ ግንኙነት፡ «በዕድል፡ ደረጃ» ተወስኗልና። የሚቃወሙት፤ አንዳንድ፡ ሁናቴን፡ አንዳንድ፡ ገዢዎችን፡ ነው፡ ኸየግል፡ ቂም፡ ያደርጉታል።

የአስተማሪዎች፡ ስብሰባ፡ እንዲሁ፡ በዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ሆነ። አስተማሪዎች፡ አዳራሻቸው፡ ቁጭ፡ አሉ። ዲሬክተሩ፡ መጣና፡ ለምን እታስተምሩም? አላቸው። ዝም። ጥያቄውን፡ ደገመ። ዝም። ሆኖ፡ በኋላ፡ አክሊሉ፡ ሀብቴ፤ የመምህራን፡ ፕሬዚዳንት፡ መጣ። ጠየቀ። ጮሁ። ውጣ—ውጣ—ከዚያ፡ አቶ፡ ወርቁ፤ የአዲስ፡ አበባ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ሥራ፡ መሪ፡ መጡ። ጠየቁ። ዝም፤ ዝም፡ ሆኖ፤ የፅጥታ፡ መሪ፡ ድረሴ፡ ዱባለ፡ መጣ። ጠየቀ። ከመቀመጫውም፡ የተነሳ፡ አልነበረም። ተናገሩ፡ ተባለ። ማታቸውን፡ ብቻ፡ በዝምታ፡ አወዛወዙ፡ አሉ። ቢቸግር፡ የአዲስ፡ አበባ፡ አስተማሪዎቹ፡ መሬ፡ ከተፈሪ፡ መኰንን፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እንዲመጡ፡ ተጠየቁ። መጡ። አዳራሹ፡ ገባ። አሳብ፡ ለአሳብ፡ ከተለዋወጡ፡ በኋላ፡ የአሁኑ፡ ሥራ፡ ማቆም፡ ለትግላቸው፡ እንቅፋት፡ መሆኑን፡ ስለገለጠላቸው፡ ወዲያው፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ሥራ፡ ጀመሩ።



## ዘመናዊ፡ መኳንንትና፡ የፊውዳሉ፡ ሥርዓት

ከይኽሱ።

በበሰበሰው፡ የኢትዮጵያ፡ ፊውዳለ—ሥርዓት፡ ውስጥ፡ «መኳንንት» የሚለው፡ ቃል፡ ምን፡ ማለት፡ እንደሆነና፡ እነማንን፡ እንደሚያመለክት፤ ለማንም፡ ግልጽ፡ ነው። ስለዚህ፡ ይህን፡ ቃል፡ ከሥረ—መሠረቱ፡ ማስረዳት፡ አስፈላጊ፡ አይመስለኝም።

ዘመናዊ፡ መኳንንት፡ የምንላቸው፡ ከባላባቶችና፡ ከባለሀብቶች፡ ወገን፡ የተወለዱ፤ አንዳንድ፡ ከሠራተኛውና፡ ከገበሬው፡ መሐከል፡ የፈለቁ፤ ዛሬ፡ ለጊዜው፡ የፊውዳሉን፡ መንግሥት፡ ቢሮክራታዊ፡ መኪና፡ የሚያኪያሂዱ ከፍተኛ፡ ባለሥልጣኖች፤ ከፍተኛ፡ ነጋዴዎችና፡ ባለፋብሪካዎች፡ ኢትዮጵያውያን፡ ናቸው። ዘመናዊ፡ ያሰኛቸው፡ የጊዜውን፡ የምእራብ (የቡርዡዋ)፡ ኢዲዎሎጅ፡ በትምህርት፡ ቤት፡ አግኪይነት፡ ቀድተው፡ ከወላጆቻቸው፡ ከወረሱት፡ አስተያየት፡ ጋር፡ የተቀላቀለ፡ ርእዮተ—ዓለም፡ ስላላቸው፡ ነው።

የአንድ፡ ዘመናዊ፡ መኳንንት (ኢትዮጵያዊ)፡ ኑሮ፤ አስተያየት፤ ወይም፡ ጠቅላላ፡ የሕይወት፡ ይዘት፡ ምንድነው? ተብሎ፡ ቢጠየቅ፡ የሚገኘው መልስ፡ የሚያስደንቅ (የሚያስቅ)፡ ነው። በደፈናው፤ አሁን፡ በሚገኝበት፡ አሰፋፈር፡ ሁኔታ፡ ውስጥ፤ መቸም፡ የሙሉ፡ ተሳታፊነት፡ ስፍራ፡ አልተፈቀደለትም፤ አሳቡን፡ አይጠየቅም፤ አሳብም፡ የለውም፤ ለግላዊ፡ ጥቅሙና፡ ለሆዱ፡ ብቻ፡ የሚገዛ፡ ሥልጡን፡ አገልጋይ፡ ነው። ይኸም፤ እርግጥ፤ ታሪካዊ፡ ምክንያት፡ አለው። አንድ፡ ትውልድ፡ የተቀዳሚውን፡ ትውልድ፡ ርእዮተ—ዓለም፤ ምኞትና፡ ተስፋ፡ ወዘተ፡ ከፋም፡ ሆነ፡ ደግ፡ ከጥላ፡ ጉደል፡ ይወርሳል። በኢትዮጵያ፡ ያሁኑ፡ ትውልድ፡ ህሊናው፡ ከሚያመለክተው፡ ይልቅ፡ ልምድ፡ መከተልን፤ ለበላይ፡ መታዘዝን፤ በጠባቡ፡ ለራስና፡ ለቅርብ፡ አዝማድ፡ ብቻ፡ ማሰብን፤ ይኸንንም የመሳሰለውን፡ ሁሉ፤ ከአለፈው፡ ወርሷል፤ ማለት፡ መንፈሱ፡ ጨርሶ፡ ነፃ፡ ስላልሆኑ፡ የልማድን፡ ሰንሰለት፡ ሰብሮ፡ ለአሁኑ፡ ጊዜ፡ ተፈላጊ፡ የሆነውን፡ ተግባር፡ ለመፈጸምና፡ ከግለ—ሰባዊ፡ የራቀ፡ ሀላፊነትን፡ ለመረከብ፡ አልቻለም (ቆርጦ፡ አልተነሳም)፤ አልደፈረም። ከዘመናዊ፡ መኳንንት፡ ውስጥ፡ አንዳንድ፡ ያሁኑን የኢትዮጵያን፡ ሁኔታ፡ በትክክል፡ ለመረዳት፡ የቻሉ፡ አይጠፉም። ሆኖም፡ የያ

ሚዎች)፡ሆነው፡የተነሱ፡ሁሉ፡እንደወንጀለኛ፡እየተያዙ፡ይደበደባሉ።ለምሳሌ፡የአዲስ፡አበባ፡ተማሪዎች፡ሥራ፡የሌለው፡ሥራ፡ያግኝ፤ጢሰኛው፡ገበሬ፡የሥራዉን፡ፍሬ፡መነጠቁ፡ይቁም።ብለዉ፡ከድሀው፡ወገን፡ስለተሰለፉ፤እንደዚሁም፡ታደሰ፡ብሩ፡ጢሰኛው፡ገበሬ፡የመሬቱና፡የሥራዉ፡ፍሬ፡ባለቤት፡ይሆን፡ዘንድ፤የፊውዳል፡አለቆች፡ከድሀው፡ጫንቃ፡ላይ፡ይውረዱ፡ብሎ፡ስለተነሳ፤የደረሰባቸውን፡ማንም፡ያውቀዋል።ዕውነቱን፡ሠፊው፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡እንዳያውቀው፡ስለተፈራ፤እንዳዘዙት፡የሚበይነው፤ለጥቅም፡መጠበቂያና፡ለማጭበርበሪያ፡የቆመው፡ፍርድ፡ቤት፡ታደሰ፡ብሩን፡ሊያናግረው፡የቻለው፡በሩን፡ዘግቶ፡ነው።የሥራውን፡ፍሬ፡እየተገፈፈ፡በበሽታ፡በረሃብና፡በችግር፡እየተቆራመደ፡እንጀቱን፡አጥፎ፡የሚተኛው፡ከልታማው፡ገበሬና፡የተበዘበዘው፡ሠራተኛ፡ይህንሁሉ፡አይስተውም።

የሕብረተሰብ፡አቋም፡የሚመነጨው፡ከኢኮኖሚው፡አቋም፡ስለሆነ፤ሥርዓት፡ኢኮኖሚውን፡ሳይነኩ፤ባለሥልጣኖችን፡ብቻ፡መለዋወጥ፡መሻሻልን፡አያመጣም።በ፲፱፻፷ ዓ·ም·ቁጥራቸው፡በርከት፡ያሉ፡የፊውዳሉ፡ሥርዓት፡መሪዎች፡የተወገዱና፡ያረጀው፡ሥርዓትም፡አስተዳደር፡ከዚያ፡በሬት፡ደርሶበት፡በማያውቅ፡አኳኋን፡የተጋለጠ፡ቢሆንም፤ይኸው፡ዛሬ፡እንደገና፡ክፍት፡የሆነውንም፡ቦታ፡በሁለትና፡ሦስት፡እጥፍ፡በሌሎች፡ተክቶ፡ጭቆናውን፡ቀጥሏል።ማንም፡ሰው፡ምስጥ፡በበላው፡ምሰሶ፡ላይ፡አዲስ፡ቤት፡አይሠራም፡ይህን፡መሰዪንከንቱ፡የሆኑ፡አሳሳች፡ወሬ፡የሚሰብኩ፡ከሁለቱም፡ዓለም፡መጠቀም፡የሚፈልጉ፤የያዙት፡እንዳይረጋገጡ፡ወደተሻለ፡ምቾት፡ለመሻገር፡የሚመኙ፡አድርባይ፡ዘመናዊ፡ብቻ፡ናቸው።

የፊውዳሉ፡ሥርዓት፡ከመሠረቱ፡ተለዉጦ፡በሠራተኛዉና፡በገበሬዉ፡ጥቅም፡ላይ፡የተመሠረተ፡ሕዝባዊ፡አስተዳደር፡ካልቆመ፡በስተቀር፡የላብአደሩ፡ኑሮ፡ሊሻሻል፡አይችልም።እንደረመጥ፡እሳት፡የተዳፈነዉ፡የላብአደሩ፡ሕዝብ፡ሬቮሉሽናዊ፡ኃይል፡የተሚነዉን፡ሥርዓት፡ከነዝባዝንኪዉ፡በታትኖ፡በመጣል፡የራሱና፡የሀብቱ፡ባለቤት፡ለመሆን፡እንደሚበቃ፡ጥርጥር፡የለዉም።



## የመንግሥቱን፡ጋዜጦች፡ስናገላብጥ፤

## የትምህርት፡ነፃነት፡ለኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በሙሉ

ሰሞኑን፡የትም፡ቤቶች፡መከፈቻ፡ጊዜ፡በመሆኑ፡የመንግሥቱ፡ጋዜጦች፡በሙሉ፡በዚሁ፡ጉዳይ፡ትችትና፡ወሬ፡ይዘው፡ነበር።ይለፈልፋሉ፤ይለፈልፋሉ፤ግን፡አንድም፡የሚሉት፡ነገር፡የላቸውም።አንዳንዴ፡ተሳስተው፡(ቁም፡ነገር)፡ያወሩ፡እንደሆነ፡የመንግሥታቸውን(የቀጣሪያቸውን)፡ሙያ፡ለመዘርዘር፡እንጅ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በዚህ፡በኩል፡ለገጠመው፡ችግር፤እንኳን፡ቀዋሚ፡መፍትሄ፡ሊሰጡት፤ለብዙ፡ዘመናት፡ያስለመዱን፡ስንኩል፡የሆኑ፡ምስለ፡መፍትሄ፡እንኳን፡ተስኗቸዋል።

ጭንቃቸውን፡ለሄራልድ፡ጋዜጠኛ፡ያዋዩ፡አንዲት(ሰባት፡አባት፡የሞተባቸው፡ሰባት፡ህጻናት፡የሚያሳድጉ)፡ድሃ፡እናት፡ያሉትን፡መስማት፡ብቻ፡ጊዜው፡የመላ፡ኢትዮጵያ፡ወጣቶችና፡ወላጆች፡የሰቀቀን፤የለቅሶ፤የትካዜ፡መቁረጥና፡የቁጣ፡ጊዜ፡መሆኑን ኣበጥሮ፡ያሳያል።ጋዜጠኛው፡ደህና፡እርጎ፡ያቀርበዋል፡እሱን፤እንስማ

«የትምህርት፡ዕድል፡ደርሶኝ፡አያውቅም።ስለዚህ፡ዘልዓለሜን፡በድንቁርና፡እኖራለሁ።ታዲያስ፤ልጆቼም፡እንደዚሁ፡ደንቁረው፡ሊቀሩብኝ፡ነወይ?»ይኸን፡አሰቃቂ፡ታሪካቸውን፡እንባ፡እያቃናቸው፡የሚያዋዩን፡የልጆቻቸው፡አባቶች፡ሞተውባቸው፡ሰባት፡ልጆቻቸውን፡በግርድና፡ተቀጥረው፡የሚያሳድጉ፡እናት፡ናቸው።

ይህም፡ሆኖ፡ታዲያ፡መንግሥታቸው፡ችግሩን፡ለማስወገድ፡ከተአምር፡መለስ፡የሆነው፡ኹሙከሬ፡ሁሉ፡እንደሚያደርግ፡ሊያረጋግጡልን፡ጋዜጦቹ፡በሙሉ፡ይወድቃሉ፡ይነሳሉ።እዚህ፡ላይ፡ታዲያ፡ዋናው፡ችግር፡ዘለው፡ላይ፡ላዩን፡እያንዣበቡ፡የሚዘባርቁትን፡ፍሬቢስ፡አሉባልታ፡ስናነበው፡ነገሩ፤በየዓመቱ፡የትምህርት፡ዕድሚያቸው፡እየተላለፈ፡የልጆቹ፡እናት፡እንዳሉት፡«በድንቁርና፡ታስረው»፡ወደዘለዓለም፡ጨለማ፡የሚጉርፉትንበሚሊዮን፡የሚቆጠሩ፡ወጣቶችን፡የሚመለከት፡አሳዛኝ፡ጉዳይ፡ባይሆን፡ኖሮ፡በሳቅ፡ይገድለንነበር።

ከኢትዮጵያ፡ወጣቶች፡ለምን፡ከመቶ፡ዘጠና፡እጅ፡በላይ፡የትምህርትን፡ብርሃን፡ሳያዩ፡«በድንቁርና፡ታስረው»፡ይቀጣሉ?በትምህርት፡ገበ

ታስ፡ላይ፡ያሉት፡የድሃ፡ልጆች፡ለምን፡በየምክንያቱ፡እየተፈናቀሉ፡ይወጣሉ «ፈተና፡ወደቃችሁ»፡ተብለው፡ትምህርት፡የተከለከሉት፡ወጣቶች፡የት፡ደረሱ? ለምንስ፡ይህን፡ያህል፡ወደቃችሁ፡ይባላሉ? ዩኒቨርርም፡የላችሁም፡ተብለው፡በድህነታቸው፡ብቻ፡ከትምህርት፡ቤት፡የተፈናቀሉት፡ሕጻናት፡ምን፡ቀጣቸው? እንኳንድ፡የውጭ፡አገር፡መንግሥታት፡በነፃ፡ትምህርት፡እንስጥ፡እያሉ፡አፍ፡አውጥተው፡እየለመኑ፡ህገራቸው፡«በታጠፋ»፡እየተባሉ፡ትምህርት የተነፈጉት፡ወጣቶች፡እየወጡ፡እንዳይግሩ፡መንግሥቱ፡ለምን፡ሥራዬ፡ብሎ፡እንቅፋት፡ይሆናል? እነዚህ፡የኛ፡ብቻ፡ሳይሆኑ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በሙሉ፡የቁጣ፡«ዕንባ፡እያነቀው»፡የሚያቀርባቸው፡ጥያቄዎች፡ናቸው። ነገር፡ግን፡የመንግሥቱ፡ጋዜጦች፡አይነኳቸውም፤ ቢያልፉ፡ቢነኳቸውም፡የሚሰጡን፡መልስ፡በተስፋ፡መቁረጥና፡በልፍስፍስነት፡መንፈስ፡የተሞላ፡ስለሆነ፡እርገጠኛውን፡መፍትሄ፡ከነሱ፡አናገኘውም። እነሱን፡እናናግራቸው።

በሰንደቅ፡ዓላማ፡አዘጋጅ፡በአቶ፡ያሬድ፡ጎ፡ሚካኤል፡እንጀምር። ወግነው፡ለዚህ፡ጉዳይ፡«ራስን፡በራስ፡ለማስተማር»፡ብለው፡በርዕሱ፡እንቀጽ፡መልክ፡ሰፋ፡ያሉ፡ትችት፡አቅርበውልናል። ግን፡ጀምረው፡እስከሚጨርሱ፡ድረስ፡እላይ፡ከየናቸው፡ጥያቄዎች፡አንዱንም፡እንኳን፡ጠለቅ፡አድርገው፡አይነኩም። የችግሩን፡መሠረት፡አያዩትም፤ መፍትሄውን፡አይሰጡንም። እህ ታዲያስ? እሳቸውን፡እንስማቸው።

«ከዚህ፡ቀደም፡በዚሁ፡ጋዜጣ—መውደቅና፡መነሳት—በሚል አርዕስት፡ለወላጆችና፡ለተማሪዎች፡የሞራል፡ድጋፍ፡ይሆን፡ዘንድ፡ልዩ፡መልዕክት፡ማስተላለፋችን፡ይታወሳል።» በአቶ፡ያሬድ፡የሞራል፡ድጋፍ፡መልእክት፡«ከወደቃችሁ፡በኋላ፡ፈተና፡ያለፋችሁ፡ከትምህርት፡ቤት፡ከተባረራችሁ፡ኋላ፡በመንገድ፡ስትንቀዋለሉ፡ያለ፡ዘመድ፡ሥራ፡ያገኛችሁ፡ከመቅጽበት፡በታ፡ተገኝቶ፡የትምህርት፡ዕድል፡ያገኛችሁ፡ወንድሞች፡እንዳላችሁ፡አደራ፡ድምጻችሁን፡እንድታሰሙን።» የአቶ፡ያሬድ፡መቀባጠር፡እዚህ፡ላይ፡አያበቃም። የሳቸው፡«የሞራል፡ድጋፍ»፡በስንኩሉ፡መንግሥት፡የተቆጣውን፡ሕዝብ፡እንደማያበርደው፡የተረዱት፡አይመስልም። እንዲያውም፡አልፈው፡ተርፈው፡በዚህ፡አሳዛኝ፡ሁኔታ፡ሕዝቡ፡ማዘን፡መቆጣቱን፡ትቶ፡ሊደሰትበት፡የሚገባው፡ጉዳይ፡ተፍጨርጭረው፡ያገኙ፡መስሏቸዋል። እንደገና፡እናናግራቸው።



«በእርግጥ፡በዘንድሮው፡የፈተና፡መውደቅና፡መነሣት(!)፡ምክንያት፡እንደአለፉት፡ዘመናት፡ከበድ፡ያለ፡የሞራል፡ውድቀትን፡ሕይወትን በገዛ፡እጅ፡የማጥፋት፡ዕድል(!)፡ባለመድረሱ፡ማማረር፡አይገባም። ይህም፡አንድ፡ታላቅ፡ፈተና፡የማለፍ፡ምልክት፡ስለሆነ(ደግነቱ፡በዚህ፡በኩል፡መንግሥትም፡በፈተና፡ሊጥል፡አይችልም)፡ወላጆች፡ሊደሰቱ፡ይገባል። በዚህ፡እንግዲህ፡የቻለ፡ይደሰት! እኛ፡ግን፡ቀጥለን፡አቶ፡ያሬድንና፡መሰላቸውን፡ግና፡ብዙ፡እንጠይቃቸዋለን።

አቶ፡ያሬድ፡«የሞራል፡ድጋፋቸውን» ፡የደስታችንን፡ጥልቀትና ደህና፡አድርገው፡ከስጨበጡን፡በኋላ፡በሃገራችን፡ግንም፡ሊከድ፡የማይችለውን፡የትምህርት፡ችግር፡እያለሳለሱ፡ሊያስረዱን፡ይሞክራሉ። ለትምህርት፡የደረሱ፡ህጻናት፡ቁጥር፡እያደገ፡ቢሄድም፡እሳቸው፡እንደሚሉት፡«በዚያም በዚያም፡ሆነ፡ለአዲስ፡ገቢ፡ተማሪዎች፡የትምህርት፡ዕድል፡ማግኘት፡አጠራጣሪ፡ሆኗል»(አቶ፡ያሬድ፡እግዚር፡ይስጥልን፤ የርስዎን፡ሞራል፡ድጋፍ፡በናገኙ፡ኖር፡እንዲህ፡ዓይነቱን፡አሰቃቂ፡መርዶ፡የኢትዮጵያ፡ወጣቶችና፡ወላጆች እንዴት፡አድርገን፡እንችለው፡ነበር?)፤ ግን፡እርስዎ፡እንደሚያለሳልሱት፡ጉዳዩ፡«አጠራጣሪ»፡ብቻ፡አይደለም። በእርግጥ፡የሚታይ፡መቅሰፍት፡መሆኑን፡እርስዎ፡እንደሚሉት፡«ወላጆች፡ከልጆቻቸው፡ጋር፡ደጅ፡ሲጠኑ፤ ማለት፡ልጆቻችንን፡ተቀበሉን፡እያሉ፡ሲማልዱ፡»የሚያዩት፡መራራ፡ዕውነትነው! አወን፡አቶ፡ያሬድ፡በሚሊዮን፡ለሚቆጠሩ፡ወንድሞችና፡እህቶቻችን፡የትምህርት፡በርሃን፡ማግኘት፡«አጠራጣሪ»፡ሆኗል። ይህንንም፡ያመኑልን፡እርስዎ፡ብቻ፡አይደሉም።

የኢትዮጵያን፡ድምፅ፡እናዳምጠው። «በመላው፡የንጉሡ፡ነገሥቱ፡ግዛት፡ዕድሜያቸው፡ለትምህርት፡የደረሰ፡ሕጻናት፡ቁጥር፡ወደ፡አራት ሚሊዮን፡መድረሱን፡ዩኔስኮ፡በአቀረበው፡ራፖርት፡አመለከተ። ከነዚህ፡ውስጥ፡ትምህርት፡ቤት፡ያገኙ፡ግን፡ከመቶ፡አስራ፡ሁለት፡ብቻ፡ናቸው፡ሲል፡ራፖርቱ፡ጨምሮ፡አስረዳ።» እዚህ፡ላይ፡ልብ፡እንበለው! የሚወራው፡ስለሕጻናት፡ብቻ፡ነው፤ ጠቅላላ፡የትምህርት፡ዕድሜ፡ያላቸው፡ወጣቶች፡ግን፡በኢትዮጵያችን፡ከ፲፩ ሚሊዮን፡በላይ፡መሆናቸውን፡አቶ፡መርስዔ፡ሐዘን፡ስታቲስቲክዎን እንደገና፡ቢያገላብጡት፡ይረዱታል።(፩) ከዚህ፡በኋላ፡አቶ፡መርስዔ፡ሐዘን፡የተለመደውን፡«ዕምነት»፡ይቀጥሉልናል። «የትምህርት፡ፈላጊዎች፡ብዛት



(፩)፡ገጽ፡፳፫፡ተመልከት

ከዕለት፡ወደ፡ዕለት፡እየጨመረ፡በመሄዱ፡አሁን፡ያሉት፡ትም፡ቤቶች፡የሕጻ
ናቱን፡ፍላጎት፡ግርከት፡አይችሉም።» አቶ፡መርስዔ፡ሐዘን፡ሐዘናችንንየም
ንረሳበትና፡የምንጽናናበት፡ተስፋ፡ሳይወረውሩልን፡ሊያልፉ፡አይሞክሩም
ቀጠል፡ያደርጉና፡ለሚመጣው፡ዓመት፡አይዞዋችሁ፡ሲሉን፡«የሕጻናቱ፡ቁ
ጥር፡በአሁኑ፡ይዞታ፡እየቀጠለ፡ከሄደ(በ፲፱፻፺፪ ዓ·ም)፡በ፩ኛ፡ደረጃ፡ብቻ(!)
ከ፰፻፶፡በላይ፡የሆኑ፡ተማሪዎች፡ይኖራሉ»።ያስገቡትዎት፡አቶ፡መርስዔ፡ሐ
ዘን፤ለሙከራዎ፤እኛ፡ግን፡መጽናናት፡አንችልም።እርስዎ፡የሰጡንን፡ተስፋ፡
ቶሎ፡ብለን፡በምንጠብቅበት፡በአንድ፡ዓመት፡ውስጥ፡በኢትዮጵያ፡፴፻፶፡
ሕጻናት፡እንደሚወለዱ፡የጥቅምት፲፡ቱ፡ሄራልድ፡ገልጾልናል።ደግሞ፡ይህ፡
«ከ፩ኛ፡ደረጃ፡ብቻ፡፰፻፶፡» ብለው፡የሰጡት፡ተስፋ፡ብዙ፡ሳንርቅ፡ከጎረቤት፡
አገሮች፡ጋር፡እንኳን፡ብናመዛዝነው፡በጣም፡ዝቅተኛ፡ሆኖ፡እናገኘዋለን።ለ
ምሳሌ፡በእህት፡አገራችን፡በኬንያ፤«በ፩ኛ፡ደረጃ፡ብቻ፡» በዚሁ፡በያዝነው፡ዓ
መት፡ተመዝግበው፡የሚገኙት፡የሴቶች፡ወጣቶች፡ቁጥር፡ብቻ፡ያገራችን፡
ለመጪው፡ዓመት፡በተስፋ፡ታስተምራለች፡ከሚሉን፡ከወንድና፡ከሴት፡
ጠቅላላ፡ድምር፡አሳምር፡ይበልጠዋል።እዚህ፡ላይ፡መርሳት፡የሌለብንየኬን
ያ፡ሕዝብ፡ቁጥር፡፲ ሚሊዮን፡ሲሆን፡የኢትዮጵያ፡ወደ፴፫ ሚሊዮን፡ግድም፡
መጠጋቱንነው።

ይበልጥ፡ደግሞ፡አቅሙን፡የሄራልዱ፡አቶ፡አሰግድ፡ብጥር፡አደ
ርገው፡ያስረዱናል።«ዳግማዊ፡ምኒልክ፡ትም፡ቤት፡አኩልኩለው፡ለመመዝ
ገብ፡ከሚጠይቁት፡፩፻፡ሕጻናት፡፩ መቶ፡ብቻ፡የመመዝገብ፡ዕድል፡አግኝተ
ዋል።» ይሉንና፡እንደዚህ፡ዓይነት፡ችግር፡ቢፈጠር፡የመግር፡መብት፡በተነፈ
ጉት፡ሕጻናት፡«ዕድለቢስነት» እንጅ፡ችግሩ፡ም፡ሆኑ፡መፍትሄው፡ከጠቅላላው፡
ከሃገሪቱ፡ባላባታዊ፡አጽም፡ጋር፡ምንም፡ዓይነት፡ግንኙነት፡ሊኖረው፡እንደማ
ይችል፡«ሊያብራሩልን፡» እንደመሰሎቻቸው፡ሞከሩ፡ነገርትተው፡ፍሬከ
ርስኪ፡ይተቻሉ።«ዕድለ፡ቢሶቹ፡አንባቸውን፡እያፈሰሱ፡ወደየቤታቸው፡ተ
መልሰዋል፤—ጉዳዩን፡በደንብ፡ስለሚያውቁት—እንደገና፡ሌላ፡ቢታ፡መሞ
ከራቸው፡አይቀርም፡ብዙ፡ግን፡አንዳንዶቹ(አቶ፡አሰግድ፡አንዳንዶቹ፡ሲሉ፡እ
ከ፲ ሚልዮን፡በላይ፡የሚሆኑ፡የሃገራችንን፡ወጣቶች፡ብለን፡እናነብባቸው፡)፡
የመመዝገብ፡ዕድል፡እንደማያጋጥማቸው፡የታወቀነው።» አቶ፡አሰግድ፡እ
ንዲህ፡የሆነበትን፡ምክንያት፡ሊያብራሩልን፡ይጣጣራሉ።እያያዛቸው፡ከመን



ግሥቱ፡ምንም፡ዓይነት፡ጉድለት፡እንደሌለ፡ለማሳመን፡በመሆኑና፡የችግሩን
መሠረት፡ከሌላ፡ሸርኩቻ፡ፈልፍለው፡ማውጣት፡ስላለባቸው፡እንዲህ፡እያ
ሉ፡ያሽሙጥጣሉ።«ይህ፡የሆነበት፡ምክንያት፡በየዓመቱ፡የሚወለዱት፡ሕ
ጻናት፡ቁጥር፡በጣም፡ስለበዛና፡እነሱንም፡ለመቀበል፡ያሉት፡ትም፡ቤቶች፡ቁ
ጥራቸው፡ስለማይጨመር፡ነው።» ዞሮ፡ዞሮ፡«ሕጻናት፡በዙ» ሊሉኙነው።አስ
ተሳሰባችውን፡የተከተልነው፡እንደሆነ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡የትምህርት፡
ችግር፡መፍትሄው(የትም፡ቤቶች፡«ቁጥራቸው፡ስለማይጨር»)ሕጻናትን፡
በመቀነስ፡ብቻ፡ነው፡ሊሉን፡ነው።አትወለዱ፡አይበልም! አትደጉ፡አይበል
ም! እህ፡ታዲያስ? ለጊዜው፡መንግሥቱ፡ሕጻናትን፡ለመቀነስ፡ያገኘው፡ዘዴ
ትም፡ቤቶች፡ደጃፍ፡ፖሊሶቹን፡አቁሞ፡በታላቅ፡ጉጉት፡ከያለበት፡የሚጎርፉ
ትን፡ሕጻናት፡ከነወላጆቻቸው፡እየጠረጉ፡መመለስ፡ነው።ይህ፡የተደረገ፡ጉዳ
ይነው።ወደፊትም፡ይቀጥላል፤የባላባታዊው፡መንግሥት፡እስከለ፡ድረስ።

አቶ፡አሰግድን፡እንከተላቸው።ይህ፡የመተፋፈግ፡ችግር፡ያለው
በመጀመሪያ፡ደረጃ፡ብቻ፡ሳይሆን፡ወጣቱን፡ኢትዮጵያዊ፡በያለበት፡ይከተለ
ዋል።ትም፡ቤት፡ከተመዘገበም፡በኋላ፡አይለቀውም።ገብተዋልና፡እንዳይገ
ቡ፡በር፡መዝጋት፡አይቻልም! ታዲያስ? የመውጫውን፡በር፡በሰፊው፡መክ
ፈት፡ነዋ! እዚህ፡ላይ፡መንግሥቱ፡የሚከተለው፡መስመር፤«የማንም፡ልጅ»
እንዳይግር፡ወጣቱን፡በየምክንያቱ፡ተስፋ፡እያስቆረጡና፡እያሰናከሉ፡ከት
ምህርት፡ገበታ፡ማፈናቀል፡ነው።ከሚያስፈልገው፡ግሬያና፡ደጅ፡ጥናት፡ሌላ፡
ደግሞ፡የድሃው፡ልጅ፡ከታወቀው፡የትምህርት፡ወጭ፡በላይ፡በተጨማሪ፡ብ
ዙ፡ሌላ፡ወጭ፡እንዲያደርግ፡ይገደዳል።እርስዎ፡እንደሚሉት፡«የዩኒፎርም
ችግር» የሚባለው፡አለ።የኢትዮጵያ፡ወጣቶች፡ንፁሕ፡ቢለብሱ፡ቢያምርባ
ቸው፡ደስታችን፡ነው፤ግን፡አሁንም፡እርስዎ፡እንደሚሉት፡«የአንዳንድ፡ቤ
ተሰቦች፡ጠቅላላ፡ገቢ፡ከአንድ፡ዩኒፎርም፡ዋጋ፡ያነሰ» ሲሆንስ? የአንድ፡ዩኒፎ
ርም፡ዋጋ፡ከጠቅላላው፡የቤተሰብ፡ገቢ፡በልጦ፡ሲገኝ፡ሁለት፡ሦስት፡አራት፡ል
ጆቹን፡ዩኒፎርም፡አልብሶ፡ለማስተማር፡የሚገደደው፡ቅጥሠራተኛና፡ድሃ፡የ
ልጆች፡አባት፡የት፡ይድረስ? ይህ፡እኛ፡በሃሳባችን፡ውስጥ፡የፈጠርነው፡ሳይሆ
ን፡ያለና፡የሚታይ፡ችግር፡ነው።እዚህ፡ላይ፡እንደገና፡ደግሞ፡አንድ፡«ሰይቸን
ቶ» ነጅ፤የልጆች፡አባት፤ለሄራልድ፡ዜና፡አቅራቢ፤ያዋየውን፡እንስማ፤«ወን
ድም» አለ፡ሰይቸንቶ፡ነጅው፤ቁጣና፡ሐዘን፡ጉርሮው፡ን፡አፍነው፡ይዘውት፤

«አራት፡ልጆቼ፡ከትምህርት፡ቤት፡ተባረሩብኝ፤ምክንያቱም፡ለሁሉም፡አንድ፡ጊዜ፡ዩኒፎርም፡መግዛት፡በፍጹም፡ተሳነኝ።»እርስዎ፡በቀላሉ፡የዩኒፎርም፡ችግር፡የሚሉት፡እንደዚህ፡ዓይነቱን፡የማይበገረውን፡የድሃ፡ልጆች፡ጠላት፡ነው የተገኘውን፡ለብሰው፡እንዳይማሩ፡በዚሁ፡ብቻ፡«ተማሪዎች፡ሁሉ፡ዩኒፎርም መልበስ፡አለባቸው»እየተባለ፡የትምህርት፡በር፡ይዘጋባቸዋል።

ልግር፡ብሎ፡የሚጣጣር፡ኢትዮጵያዊ፡የሚያጋጥመው፡የእንቅፋት፡ዝብዝብ፡እዚህ፡ላይ፡አይወሰንም።አቶ፡አሰግድን፡እንደገና፡እንከተላቸው፤»የዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፡ደግሞ፡ችግር፡አለባቸው፤እያንዳንዱ፡ተማሪ፤ሲመዘገብ፡፳፭፡ብር፡መክፈል፡አለበት።ተማሪዎቹ፡ይህን ፡የሃያ፡አምስት፡ብር፡ራስ፡ምታት፡በለው፡ይሰይሙታል።ብዙዎቹ፡ይህን ፡ያህል፡ገንዘብ፡የላቸውም።»እርግጥ፡ይህም፡አንድ፡ችግር፡ነው።አቶ፡አሰግድ፡እንግዲህ፡ይህንን፡የዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፡ዋና፡ችግር፡አድርገው፡እዚህ፡ላይ፡ሊሰናበቱን፡ይፈልጋሉ።መቸም፡ላይ፡ላዩን፡ነካ፡ነካ፡ነውና፡ስለዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፡ችግር፡ሲያወሩ፡እዚህም፡ከሌሎቹ፡ደረጃዎች፡ይልቅ፡«ተማሪ፡በዛ፡»እየተባለ፡የሚቀነስበትን፡ዋና፡መማሪያ፡ረስተውት፡ያለፉ፡ይመስላል።ፈተና፡ስለሚሉት፡ጉዳይ፡ምንም፡አያወሩም።በሌላ፡ቦታ፤በሌላ፡አርዕስት፡ሥር፡ነካ፡ቢያደርጉትም፡ያው፡የፈተና፡መውደቅ፡በተማሪዎች፡ጥፋት፡እንጅ፡መንግሥቱ፡ሥራዩ፡ብሎ፡ይዞ፡«የማንም፡ልጅ፡»እንዳይማር፡የሚጠቀምበት፡የመቀነሻ፡መሣሪያ፡እንዳይደለ፡ሊያስረዱን፡ይሞክራሉ።እሳቸውን፡እናዳምጣቸው።እህ? ተማሪዎች፡ከሚወድቁበት፡አንዱ፡ምክንያት(ሌሎቹን፡አይሰጡንም)፡ዩኒቨርሲቲ፡ሲደርሱ፡ግራ፡መጋባታቸውና፡በቶሎ፡አለመለማመዳቸው፡ነው፡ከሉ በኋላ፡እንዲያውም፡ሲያሾፉብን፡ተማሪዎቹ፡የሚወድቁት«—አዲስ፡የጃኪሎው፡ሕንፃ፡እንደ፡ትልቅ፡ነጭ፡አውሬ፡እየተመሰለ፡ግራ፡ስለ፡ሚያጋባቸው —»ነዉ፡ይሉናል።አቶ፡አሰግድ፡እኛ፡የተማሪዎችን፡መዉደቅ፡ምክንያት፡ከዚህ፡ጠለቅ፡አድርገን፡እንፈልገዋለን።መጀመሪያ፡ግን፡በእርግጥ፡በዩኒቨርሲቲዉ፡ዉስጥ፡እርስዎ፡እንደሚሉት፡እንደነጭ፡አዉሬ፡እየተመሰለ፡ተማሪዎችን፡የሚጥል፡ነገር፡ካለ፡ለኛ፡ተስፋፍቶ፡ከሠፈረዉ፡የያንኪ፡ኢምፔሪያሊዝምና ፡«ከነበልጠቶር»፡ግብረ፡አበሮቹ፡በስተቀር፡ሌላ፡አይታየንም።

ወይ፡ዋና፡ነገራችን፡እንመለስና፡ፈተና፡የወደቁት፡ተማሪዎች፡አቶ፡አሰግድና፡መንግሥቱ፡በየጊዜዉ፡በሚሰነዝሩልን ፡ልክስክስ፡ምክንያ



ቶች፡ሳይሆን፡በጠቅላላው፡ይህ፡የሀብታሞች፡መንግሥት፡ሃገሪቱን፡«በድንቁርና፡እስር፡»ለረዢም፡ጊዜ፡ለመግዛት፡እንዲችል፡ሆነ፡ብሎ፡የሚከተለው ፖለቲካ፡መሆኑን፡እናውቃለን።ዛሬ፡በሃገራችን፡ፈተና፡የምትለውን፡የዕውቀት፡ማስናከያና፡መግቻ፡እንጅ፡በፍጹም፡የዕውቀት፡መለኪያ፡መሣሪያ፡እንዳይደለ፡እናውቃለን።ለምሳሌ፡በዚህ፡በያዝነው፡ዓመት፡የዩኒቨርሲቲ፡መግቢያ፡ፈተና፡፯ መቶ፡ብቻ፡ሳይሆኑ፡፯ ሺ፡አልፈው፡ወጣቶችና፡ወላጆች፡ቢደሰቱ፡መንሥግቱ፡ምን፡ያህል፡በከፋውና፡ምን፡ያህል፡በጩነቀው፡ነበር።የሚያልፉት፡ተማሪዎች፡ልክ፡አስቀድሞ፡የሚወሰነው፡መጀመሪያውኑ፡መንግሥቱ፡በሰናዳው፡ቦታ(ግበት፡የፊውዳሉ፡ኢኮኖሚ፡በሚችለውና፡በሚያስፈልገው፡ልክ፡)እንጅ፡በታው፡በሚያልፉት፡ተማሪዎች፡ልክ፡እንዲጨመርና፡እንዲስተካከል፡ምንም፡ዓይነት፡ጥረት፡አይደረግም።የሚፈለጉት፡ተማሪዎች ልክ፡«ለነሱው፡ልማት፡»በሚያወጡት፡የ፭ ዓመት፡ፕላናቸው፡ተቆርጦ፡ያለቀ፡ጉዳይ፡ነው! ስለዚህ፡ነው፡የትምህርት፡ዕድል፡ሊያገኙ፡የሚገባቸው፡ተማሪዎች፡ቁጥር፡አስቀድሞ፡በባላባቱ፡መንግሥት፡ተቆጥቦ፡በመወሰኑ፡ይህን፡«ፕላኑን፡»ለማከናወን፡ምንም፡ዐይነት፡እንቅፋት፡የማይበግረው።በዚህ፡በኩል፤የተማሩትን፡ኢትዮጵያውያን፡ቁጥር፡ለመወሰን፡የሚደረገው፡ጥረት፡ገና፡በደንብ፡ላልተረዱት፡ወላጆችና፡ወጣቶች፤መንግሥቱ፡ከውጭ፡ሃገር፡በሚሰጡት፡የነፃ፡ትምህርት፡ዕድል፡ላይ፡የሚያደርገውን፡ቁጥጥርና፡ድርቅ፡ያለ፡መሰናከል፡እንዲመለከቱ፡እናሳስባለን።እስከሁን፡ከዘረዘርናቸው፡መንግሥቱ፡ከሚዘረጋብን፡መሰናክሎች፡ከሁሉ፡ዓይን፡ያወጣው፡በዚህ፡በኩል፡መንግሥቱ፡የሚያደርገው፡አሳፋሪ፡ጥረት፡ነው።ከአንዳንድ፡ሃገሮች፡በየጊዜው፡ለኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡የነፃ፡ትምህርት፡ዕድል፡በገፍ፡መሰንዘሩን፡ማንም፡አይስተውም።እዚህ፡ላይ፡እንግዲህ፡የትምህርት፡ሚኒስትራችን፡«የምልከው ሰው፡የለኝም፤ግድየለም፡እግዜር፡ይስጥልን፤አገራቸው፡ይማሩ፡»እያሉ፡ቀጥ፡አድርጎ፡እየተከራከረ፡የሚያስቀርብን፡የነፃ፡ትምህርት፡ዕድል፡ስፍር፡ቁጥር፡የለውም።በዚህ፡በኩል፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡የቀረበትን፡ጥቅም፡ለማሰስብ፡ብዙ፡ሳንዘበዝብ፡አንዲት፡ምሳሌ፡ብቻ፡እንሰጣለን።በአውሮፓ፤በአሜሪካና፡በእሲያ፡በትምህርት፡ላይ፡የሚገኙ፡ኢትዮጵያውያን፡ተማሪዎች፡ቁጥር፡ተጠቅልሎ፡ቢደመር፡ከ፩ሺ፡፱መቶ፡አይበልጥም።በሶቢየት፡ሕብረት፡ብቻ፡በትምህርት፡ገበታ፡ተሰማርተው፡የሚገኙ፡የሱማሌ፡ሬፑብሊክ፡ወጣቶች፡

ከ፪ሺ፡፫ መቶ፡በላይ፡ናቸው፡፡ብዙ፡እናውራ

እኛ፡ከዚህ፡በላይ፡ብዙ፡የምንጨምረው፡የለንም፡፡የመንግሥቱ ጥቅም፡ዋስትናው፡ሕዝብን፡በተቻለ፡አደንቁሮ፡መግዛቱ፡ነው፡ብለናል፡፡በመጨረሻ፡ለወላጆችና፡ለወጣቶች፡ልናስገነዝብ፡የምንፈልገው፡በዚህ፡የባላባቶች፡መንግሥት፡ሥር፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡የትምህርት፡ፍላጐት፡በፍጹም፡ሊረካ፡አለመቻሉን፡ነው፡፡ከሕዝብ፡በየምክንያቱ፡የሚቀፈፈው(የሚገፈፈው)ሀብት፡ለትምህርት፡ቤቶች፤ለክሊኒኮችና፡ለሌሎች፡የሕዝብ፡ኑሮ፡ማሻሻያ፡ጉዳዮች፡ከመዋሉ፡በፊት፡ለነዚህ፡ጥቂቶች፡መንደላቀቂያ፡ይረጫል፡፡እንደዚህ፡ባይሆንና፡የላቡን፡ፍሬ፡ባይቀማ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በያለበት፡ተረዳድቶ፡ለልጆቹ፡ማስተማሪያ፡የሚሆኑ፡ቀላል፡ድርጅቶች፡ማቋቋሚያ፡ሀብት ባላጣ፡ነበር፡፡የመንግሥቱ፡ሀብት፡የሚገበሰበሰው፡ከድሃው፡እየተመጠጠ፡ነው፤በድንቁርናና፡ታስሮ፡የሚገኘው፡ደግሞ፡ያው፡ድሃው፡ነው፡፡

ችግሩ፡ይህ፡ነው፡ከልን፡በኋላ፡እንደመንግሥቱ፡ጋዜጦች፡ተስፋ በማስቆረጥ፡ወይም፡«የሞራል፡ድጋፍ፡»በመስጠት፡አንለያችሁም፡፡የትምህርት፡መብት፡ለአንድ፡ሕዝብ፡መሠረታዊ፡ከሆኑት፡ነፃነቶች፡ዋናው፡ነው፡፡ታላቅ፡ነፃነት፡እንደ፡መሆኑም፡መጠን«በደጅ፡ጥናትና፡በሞራል፡ድጋፍ»ሳይሆን፡በታላቅ፡ትግል፡የሚገኝ፡የሕዝብ፡አለኝታ፡ነው፡፡ዛሬ፡የጥቂቶች፡መንግሥት፡በመሆኑ፡ትምህርት፡ለሕዝብ፡በሙሉ፡ሊደርስ፡አልቻለም፡፡አይችልምም፡፡ነገ፡ግን፡በሕዝባዊ፡መንግሥታችን፡ትምህርት፡ለህዝብ፡በሙሉ፡እንዲደርስ፡የማይቆጠብ፡ድካም፡ይደረጋል፡ብለን፡እናምናለን፡፡ዛሬ፡የባላባታዊው፡መንግሥት፡ዕድሜ፡መርዘም፡በድንቁርናና፡የታሰረ፡ሕዝብ፡የሚያስፈልገውን፡ያህል፡ነገ፡ደግሞ፡ሕዝባዊው፡መንግሥት፡እንዲቆምና፡እንዲጠነክር፡በዕዉቀት፡የታነጸ፡ሕዝብ፡ያስፈልገዋል፡፡የጭቆና፡መሠረቱ፡ድንቁርና፡ነው፤የነፃነት፡ኃይሉ፡ትምህርት፡ነው፡፡ለነፃነታችን፡እንታገል፡፡ለዚህ፡ግብ፡ተጨቋኝ፡ኢትዮጵያውያን፡በሙሉ፡ተባብረን፡ከሠራን፡የወደፊት፡ዕድላችን፡ከፀሐይ፡የበራ፡ነው፡፡

እንደና ንተጨቋኝ፡ልጆቻችሁ፡የትምህርት፡ብርሃን፡የተነፈጉ፡ወላጆች!
በየምክንያቱ፡ከትምህርት፡ገበታ፡የተፈናቀላችሁ፡ወጣቶች!
ጥቅማችሁና፡የባላባታዊዉ፡መንግሥት፡ጥቅም፡ሆድና፡ጀርባ፡ናቸው፡
ደህንነታችን፡ያለ፡ሕዝባዊ፡መንግሥት፡ዘበት፡ነው!
ከሌሎች፡ወንድሞቻችሁ፡ጋር፡ተደባልቃችሁ፡ለመብታችሁና፡ለኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ነፃነት፡ታገሉ!



ኦገስት፡፲፱፡፲፱፻፷፰

ለትግላችን፡አዘጋጅ፤

የምታዘጋጀው፡ወርሀዊ፡መጽሔት(በትክክለኛ፡አጠራር፡«ትግላችን»፡ተብሎ፡የተሰየመው)በየጊዜው፡እየደረሰኝ፡አነባለሁ፡፡የምታቀርባቸው፡ጽሑፎች፡ጠቃሚንና፡ጥልቅ፡አስተያየትን፡ያዘሉ፡ናቸው፡፡ላብዛኛው፡ያገሬ፡ሕዝብ፤የትምህርት፡ገበታ፡በመነፈጉ፤እንደዚህ፡ያሉት፡ሃሳቦች፡ስላል ተገለጡለት፤ለተገለጡለት፡ደግሞ፡እንደዚህ፡ያለውን፡መጽሔት፡የማንበብ፡ዕድል፡ነፃነት፡ስለተነፈገው፡የሚሰማኝ፡ጸጸት፡ወሰን፡የለውም፡፡

ለዚች፡ጽሑፌ፡መነሻ፡የሆነው፡ከተስፋዬ፡ተኩላ፡ስለተማሪ፡ኃይሉ፡ገ፡ዮሐንስ፡የተጻፈው፡ድርሰት(አርቲክል)ነው፡፡የኃይሉ፡በፖሊስ፡ተይዞ፡መታሠርና፡መሰቃየት፤የጨቋኙ፡መንግሥት፤ፍርድን፡እንደስንዴ፡በሚሸምትበት፡ፍርድ፡ቤት፡ውስጥ፤ከሰብአዊነትና፡ከሕግ፡ውጭ፡የሆነውን፡ፍርዱን፡በኃይሉ፡ላይ፡ለማስበየን፡መጣጣር፤አሳዝኖኛል፡፡

ጨቋኙ፡መንግሥት፡ባይገባው፡ነው፡እንጅ፡እሱ፡ያልተናገረውን፡ኀድ፡ኃይሉ፡አልተናገረም፡ነበር፡፡በኢትዮጵያውያን፡ተማሪዎች፡ዘንድ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ድህነት፡እንዲነገር፡ያልተፈቀደበት፡ምክንያት፡ኦ ደናቂ፡ነው፡፡አረመኔው፡መንግሥት፡ግን፡ከአገር፡አገር፡እየዞረ፡ለጥቅ መገንዘብ፡የሚበደረው፡በዚሁ፡በድሀ፡ሕዝብ፡ስም፡ነው፡፡ድህነቱን፤በሽተኛነቱን(ያለ፡የሌለውን፡)እንደምክንያት፡እየሰጠ፡ገንዘብ፡ከመበደር፡አላቋረጠም፡፡

ይኸ፡ነቀዝ፡መንግሥት፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ከድህነት፡እንዳይወጣ፤በተውሳክ፡ብዛት፡ሞት፡በልጅነቱ፡እየተቀጨ፡እንዲቀር፡የሚጣጣር፡መሆኑ፡አይከድም፡፡ግፈኛው፡አረመኔ፡መንግሥት፤በግልጽ፡እንደሚታየው፤የሕዝብን፡ቁጥር፡ለመቀነስ፡የሚወስዳቸው፡እርምጃዎች፡በርከት፡ያሉ፡ናቸው፡፡

—ስቅላት፤

—ወህኒ፡ቤት፡እየላኩ፡ምግብ፡መንፈግ፤

—ለግል፡ጥቅም፡ለማሠራት፡ወደ፡አዶላ፡እየላኩ፡ሰብአዊ፡ባልሆነ፡አካባቢ፡ማኖር፤ወዘተ

ይህ፡የጸና፡አቋም፡የሌለው፡መንግሥት፡የሚሠራው፡ድርጊት፡

ሁሉ፡ስህተት፡መሆኑን፡እራሱ፡በመገንዘቡ፡በዚህ፡ድሀ፡በሚባለው፡ቃል፡እየተጠቀመ፡ከሚበደረው፡ገንዘብ፡አብዛኛውን፡የሚረጨው፡ለአንዳንድ፡ወደው፡ሳይሆን፡ረሃብና፡ችግር፡አሰቃይቷቸው፡ለሱ፡ለተቀጠሩ፡ወይም፡በልዩ፡ልዩ፡ዘዴ፡ተገደው፡የሱ፡ጭፍራ፡ለሆኑ፡የግል፡ዘበኞቹ—ሲአይዲ፡ወይም፡እንዳገራችን፡አነጋገር፡ጆሮ፡ጠቢ፡ለሚባሉት—ነው፡፡ነገር፡ግን፡ልመናን፡የልማት፡መሠረት፡አድርጎ፡የማያምነው፡ኩሩው፡ያገሬ፡ሕዝብ፡ይህን፡ጠገብኩ ሰለቸኝ፡የማያውቅ፡የለማኝነት፡ጠባዩን፡እንዳያውቅበት፡ሕዝቡ፡በተማሪ፡ዘንድ፡ድሃ፡በሽተኛ፡ተብሎ፡እንዳይጠራ፡ይመኛታል፡፡ተቀርጿራ፡ከሆኑ፡ለጥቅሙና፡ለግብረአበሮቹ፡የሚያውለውን፡ገንዘብ፡ለምን፡ለሕዝብ፡ኑሮ፡ማሻሻያ፡አያውለውም፡ነበር?

ይኸ፡ስዋተኛ፡መንግሥት፡አንድ፡ቃል፡በተሰነዘረ፡ቁጥር፡እንደልማዱ፡አይደለም፡ብሎ፡የማስተባበል፡ችሎታ፡ስላነሰው፡ተማሪዎች፡ተሰለፉ፡ጽሑፍ፡በተኑ፡እያለ፡መማሪያ፡መለመኑ፡ወታደር፡ማሰለፍ፡ልማዱ፡ሆነ፡፡

ይኸንኑ፡ለማኝ፡መንግሥት፡የኢትዮጵያ፡ተማሪዎች፡ቀኑን፡አቃርበውለታል፡፡ቀኑም፡እንደተቃረበለት፡ስለገባው፡አቋሙን፡የሚቃወመው፡ወጣቱ፡ተማሪ፡በሥራ፡ገበታ፡ላይ፡መሰማራት፡እንደጀመረ፡ከደንበኛ፡አጥጋቢ፡ደመወዙ፡በላይ፡የወጭ፡አበል፤የመኪና፡መግዣ፤የቤት፡ማሥሪያ፡ወዘተ፡እያለ፡ጭማሪ(ጉቦ)፡በመስጠት፡ሊለግመጠው፡ይፈልጋል፡፡ይህም፡የመንግሥቱን፡መርበድበድና፡የሚይዘውን፡ማጣት፡በግልጽ፡ያሳያል፡፡በንደዚህ፡ዓይነት፡ወጥመድ፡እየሳበ፡ተማሪን፡ወደ፡በዝባዥ፡መደብ፡ለማስገባትና፡ከሱጉን፡በማሰለፍ፡ሕዝቡን፡በበለጠ፡ለመጨቆን፡የሚያስናዳው፡ዘዴ፡መሆኑ፡ግልጽ፡ነው፡፡

እንደዉነቱ፡ከሆነ፡ገና፡የሥራው፡ዉጤት፡ያልታየለት፡ሰው፡ይኸ፡ሁሉ፡ባልተገባውም፡ነበር፡፡ግን፡እርብትብቱ፡መንግሥት፡አስተያየት፡ግወቁና፡የጭቆናውን፡ዘዴ፡ማጥበቁ፡ነበር፡፡ነገር፡ግን፡ሕሊና፡ያለው፡ተማሪ፡ሁሉ፡በተንኮሉ፡ነቅቶበታል፡፡ባለሕሊናው፡ተማሪ፡የማይገባውን፡ክብርና፡ገንዘብ፡በመቀበል፡እየተደለለ፡ከጨቋኙ፡መደብ፡ጋር፡መቀላቀልን፡አሻፈረኝ፡ማለት፡ጀምሯል፡፡

ዙሪያዉ፡ገደል፡ሆኖ፡የጨለመበት፡መንግሥት፡ተማሪን፡እያሰቃየ፡ከትምህርት፡ገበታ፡መነጠሉ፡በበለጠ፡ቀኑን፡እያሳጠረለት፡መሄዱን፡ግ



ና፡አልተገለጠለትም፡፡ኃድ፡ኃይሉን፡የሚገፋፋው፡የሃገር፡ፍቅር፡ነው፡፡ስለዚህ፡ኃድ፡ኃይሉ፤ምንም፡እንኳን፡የሚቀበለው፡መከራ፡ለጊዜው፡የሚያሰቃይ፡ቢሆንም፤በሚያደርገው፡ትግል፡ደስታ፡እንደሚሰማው፡አይጠረጠርም

ትግሉ፡የኃድ፡ኃይሉ፡ብቻ፡መሆን፡የለበትም፡፡ትግሉ፤ኢትዮጵያ፡ከድህነት፡እንድትወጣ፤እንድትሻሻል፤ሃገሩን፡ለመሸጥ፡ከሚጣጣረውና፡ላብአደሩን፡እየገፈፈ፡በሚገዛው፤በልመና፡በገኘው፤መማሪያ፡ጉራውን፡ከሚነዛው፡ጨቋኝ፡መንግሥት፡ቀንበር፡ሥር፡ነፃ፡እንድትወጣ፤የሚጣጣር፡ኢትዮጵያውያኑ፡ሁሉ፡ነው፡፡

ኃድ፡ኃይሉ፡በርታ! ድል፡መንሻው፡ጊዜ፡ደርሷል፡፡

ከኢትዮጵያውያን፡እህቶችህ፡አንዱዋ

## ዩኒቨርሲቲ፡ለሚገቡ፡የታደሉ፡ጽሑፍ፤

የብሄራዊ፡ዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፡የኢትዮጵያን፡ሕብረተ—ሰባዊ፡አቋም፡ተንትነውና፡አበጥረው፡በመረዳት፤በዝባዦችንና፡ተበዝባዦችን፡ለይተው፡በማወቅ፡የትግል፡ወገናቸውን(ገበሬውንና፡ሠራተኛውን)፡ከመረጡ፡በርከት፡ያሉ፡አመታት፡አልፈዋል። ጨቋኙንና፡የጨቋኙ፡ወገንንም፡ከንድ፡ሁለት፡ጊዜ፡ደጋግመው፡በኃይል፡ጥምር፡ተጋፍጠውታል።ያዲስ፡አበባ፡ተማሪዎች፤በብሄራዊ፡ዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፡ማኀበር፡መሪነት፡እንደ፡—

—ድህነት፡ኃጢአት፡ነወይ?

—መሬት፡ላራሹ!

—ትክክለኛ፡ነቀፌታን፡የማይወድ፡መንግሥት፡ዘለቄታ፡የለውም፡—ወዘተ፡

ባሉት፡መሠረታዊ፡ሐሳቦች፡መሪነት፡ሰላማዊ፡ሰልፍ፡በማድረግ፡የአዲስ፡አበባን፡ሕዝብ፡ጥምር፡አነሳስተው፡መንግሥቱን፡ባጋለጡት፡ጊዜ፡የደረሰባቸውን፡መከራ፤ድብደባና፡ስቃይ፡ሁላችንም፡እናውቀዋለን።ስቃዩና፡ጭቆናው፡ግን፡ወደ፡ኋላ፡እንዲያሸገሽጉ፡አላደረጋቸውም።እንዲያውም፡የትግላቸው፡ዓይነት፡ወደ፡ከፍተኛ፡ደረጃ፡እንዲደርስ፡ረዳው።

በመጨረሻ፡የትግሉ፡መሪ፡የተማሪዎች፡ማኀበር፡የትግሉ፡አፈቀላጤ፡የተማሪዎች፡ጋዜጣ፡መሆኑን፡በመገንዘብ፡መንግሥቱ፤በአሜሪካኖች፡አሳሳቢነት፤ማኀበራቸውን፡ዘጋ(ቸው፤ጋዜጣቸውን፡እንዳያወጡ፡ከለከላቸው። ተማሪዎቹ፡ግን፡ትግላቸውን፡ቀጥለዋል።ከዚህ፡በታች፡ለአንባቢያች፡የምናቀርበው፡የብሄራዊ፡ዩኒቨርሲቲ፡ተማሪዎች፤ትግላቸውን፡በመቀጠል፤ለመጀመሪያ፡ጊዜ፡ወደ፡ዩኒቨርሲቲ፡ለሚመጡ፡እህቶችና፡ወንድሞች፤የዩኒቨርሲቲውንና፡የትግላቸውን፡ሁኔታ፡ለማስረዳት፤ያደሏቸውን፡ጽሁፍ፡ነው።

No time is so opportune as this - the time when we welcome our new progressive, well established brothers and sisters from the different high schools all over the nation - and no time is so opportune as this when we announce the ever growing force vital of the H.S.I.U. student



body.

We are welcoming you to a university which has denounced and banned the three vital student organisations, namely, U.S.U.A.A., N.U.E.U.S. and STRUGGLE, thus stripping students of their academic freedom as is granted by the University Charter.

We feel that you should be informed about the hypocritical and notorious crimes that were committed in the name of the university administration upon the student body.

The university accuses the three student organizations as being tools for political agitation on a nation-wide basis.

We wonder what these political agitations so referred to are? Should we be deprived of our unions and paper for expressing the vicious circles of our people ? That was the case of the Land to the Tiller demonstration, that was the case of the Shola Concentration Camp demonstration - that was also the case of the demonstration against the Peaceful Demonstration Proclamation Act - that was also the case of the protest against the brutal man-handling of black Africans by the white fascist Smith regime - that was the case of the anti-American-foreign-policy demonstration as expressed on the arrival of that demagogue vice President Humphrey. These were the major moves taken by the university student body - and these were the main items referred to as political agitations by the "enlightened" university administration for which it claims the "unlawfulness" of the lawful student organizations.

Let us see if these are true :

1 - Land to the Tiller demonstration was based on the unfairness of the land-owning aristocracy

on the tiller and which was and still is an economically inhumane social force which was and is responsible for the backwardness of our society.

2 - The Shola Concentration Camp demonstration which was staged by the university students in protest of the human and immoral degenerating act of the government on our fathers and mothers -who were victims of the socio-economic stand of the nation.

3 - The Peaceful Demonstration Proclamation Act, which had its root in the Shola Concentration Camp demonstration, was a direct contradiction of the constitution which is supposedly a safeguard against tyranny, mass liquidation, genocide by the few in the pursuit of their (the leaders') individual prestige and status. What are the prestige of a government - any government - its people or its individuals ?

4- The protest against the white Rhodesian regime which refuted and down-graded International Law by mercilessly executing black Africans for no apparent reason except their African nature. Is this a political agitation on a nation-wide basis if it ever is a political agitation ?

5- The protest against the masquered representative of the Johnson administration which has been exporting political unrest to Africa, Asia and Latin America.

In the hope of using the student body to achieve its own ends the university has done everything it could - but to no avail. The resistance of the student body is something that goes to prove that the university would never suceed in subduing the student body and use it to achieve its own ends, if it ever tried to - it also goes to



prove that the more the university attempts to model the intellectual grace of its students the more it obliges them to be chaotic and restless.

LONG LIVE OUR RESISTANCE! LONG LIVE OUR UNITY!

VIVA USUAA, VIVA NUEUS, VIVA STRUGGLE!

(፳)፡ በቅርቡ፡የስታቲስቲክስ፡መምሪያ፡ቤት፡ባወጣው፡መግለጫ፡የ ኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡፳፫፡ሚሊዮን፡መሆኑንና፡ከዚህም፡ውስጥ፡ከመቶ፡አርባ፡ አራቱ፡ከ፲፭፡ዓመት፡በታች፡የሚገኙ፡መሆናቸውን፡አረጋግጦልናል።